DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# የትምህርት ዓመት 2025- 2026 የምዝገባ ጥራዝ (Enrollment Packet)

ከዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ጋር በመሆን፣ ለ2025-2026 የትምርህት ዓመት (SY25-26)፣ እንኳን በደህና መጣችሁ! እባካችሁን፤ ለመጪው SY25-26፣ ይህን የምዝገባ ጥራዝ (enrollment packet) ሙሉ። ደረጃ-በደረጃ-የሆኑት ትዕዛዛቶቹ፣ ከዚህ-በታች ተካተዋል። በኦንላይን ላይ፣ ሁሉንም ሰነዶች በ[https://enrolldcps.dc.gov/](https://enrolldcps.dc.gov/) ያገኛሉ። ትርጉሞችም፤ በአማርኛ፣ በቻይኒኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በስፓኒሽ እና ቬትናም ቋንቋዎች ይገኛሉ። እያንዳንዱ ተማሪ ምንም ዓይነት የኢሚግሬሽን ሁኔታ ወይም የዜንነት ማንነት ቢኖረው፤ በሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ የመማር መብቱን፣ DCPS ለመጠበቅ በቁርጠኝነት ይሰራል። በመሆኑም፣ DCPS በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ የመኖር ብቃት ያላቸውን ሁሉንም ነዋሪዎች፣ ስለቤተሰቡ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ሳይጠይቅ ትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ገብተው እንዲማሩ ይፈቅዳል።

በDCPS ውስጥ ያለን ተልዕኮ፣ የተማሪዎቹ የቀድሞ መነሻቸው ወይም ሁኔታቸው ምንም ሆነ ምን፤ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶቻችን ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ትምህርትን በመስጠት፣ <u>ሁሉንም</u> ተማሪዎቻችንን - በኮሌጅ፣ በስራ መስክ እና በሕይወት ስኬታማ እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነው። ሁሉንም ተማሪዎች ማገልገላችን፣ ክብርን እና ደስታን የሚያጎናጽፍ ነገር ሲሆን፣ ሌላ ግሩም የሆነ የትምህርት ዓመት እንዲገጥመን በጉጉት እንጠብቃለን።

## እርምጃ 1. በዚህ ጥራዝ (packet) ውስጥ ያሉትን ቅጾች ይሙሉ

A. የመመዝገቢያ ቅጽ
B. የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ
C. የቴክኖሎጂ ቅጽ
D. መስማማት-መስጫዎች (Consents)
E. የተማሪ እና የወላጅ/አሳዳጊ መብቶች ማስታወቂያዎች
F. የዲሲ ጤና/DC Health ዩኒቨርሳል የጤና ሰርተፊኬት
G. የዲሲ ጤና የአፍ-ጤና(Oral Health) ግምገማ ቅጽ

ተጨማሪ ቅጾች፣ በሚከተለው-ላይ ይገኛሉ [https://enrolldcps.dc.gov/](https://enrolldcps.dc.gov/)።

## እርምጃ 2. ደጋፊ የሆኑ ሰነዶችዎን (supporting documents) ማሰባሰብ። ተማሪያችሁን ለማስገባት - የሚከተሉትን፣ ደጋፊ-የሆነ ሰነዶች (Supporting documents) ያስፈልጓችሁ-ይሆናል:

**ለDCPS አዲስ-የሆኑ** (*ከዚህ ቀደም የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ - በጭራሽ ተምሮ የማያውቅ*)

A. አንድ የዕድሜ ማረጋገጫ ሰነድ – ምሳሌዎቹ የሚያካትቱት፡ የልደት ሰርተፊኬት፣ የሆስፒታል መዝገቦች፣ የቀድሞ የትምህርት ቤት መዝገቦች፣ ፓስፖርት፣ ወይም የጥምቀት ሰርተፊኬት
B. የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ – ተቀባይነት ያላቸውን ሰነዶች እና ማረጋገጫ ዘዴዎችን፣ በነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጹ (*Residency Verification Form*) ላይ፣ ሙሉ ዝርዝሩን ይመልከቱ
C. የቤት ውስጥ ቋንቋ የዳሰሳ ጥናት – ይህን የዳሰሳ ጥናት ለማግኘት፣ የምዝገባ ቅጹን ይመልከቱ

**ወደ የDCPS ትምህርት ቤት፣ መመለስ**

- የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ – ተቀባይነት ያላቸውን ሰነዶች እና ማረጋገጫ ዘዴዎችን፣ በነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጹ (Residency Verification Form) ላይ፣ ሙሉ ዝርዝሩን ይመልከቱ

## እርምጃ 3. ጥራዙ(packet)ን እና ማንኛውም ደጋፊ-ሰነዶች (supporting documents)ን፣ ወደ ተማሪዎ ትምህርት ቤት - የምዝገባ ቡድን አስገቡ።

## እርምጃ 4. ነፃ እና ቅናሽ ዋጋ ያላቸው ምግቦችን (Free and Reduced-Price Meals - FARM) ማመልከቻን ለመሙላት የቀን-መቁጠሪያዎ ላይ ማስታወሻ ያድርጉ።

ለነፃ ምሣ፣ ቤተሰቡ ብቁነቱን ለመወሰን፤ የ'FARM' ማመልከቻ - ለመጪው የትምህርት ዓመት - በጁላይ (July) 1 ቀን ላይ መገኘት-የሚችል-ይሆናል። የዚህ ዓመት - የትምህርት ቤቶች ዝርዝር - ለምሣ የከፈሉ እንዲሁም ማመልከቻ-ያላቸው በዚህ ላይ - በ[https://dcps.dc.gov/farm](https://dcps.dc.gov/farm) መገኘት የሚችል፤ ወይም በትምህርት ቤታችሁ የእንግዳ-መቀበያ (front office) መገኘት-ይችላል። ይህን ማመልከቻ፤ ቤተሰቦች በየዓመቱ-ማስገባት **አለባቸው**።

በDCPS ውስጥ ምዝገባን ለሚጠይቁ እያንዳንዱ ቤተሰቦች፣ ዓመታዊ የዲስትሪክት ነዋሪነት ማረጋገጫን DCPS እንዲጠይቅ ሕጉ የሚያስገድደው መሆኑን እባክዎን ያስተውሉ። DCPS፣ የነዋሪነት ማረጋገጫውን - በምዝገባ ወቅት ያካሂዳል (የነዋሪነት ማረጋገጫው፣ ተማሪው ምዝገባውን ከጠየቀበት መጀመሪያ ቀን ጀምሮ በ**አስር የቀን መቁጠሪያ (ካላንደር) ቀናት** ውስጥ) መረጋገጥ ይኖርበታል። በዲስትሪክቱ መስፈርቶች መሠረት የዲስትሪክት ነዋሪነትዎን ማረጋገጥ ካልቻላችሁ፣ ወይም ነዋሪ-ያልሆኑ የሚከፍሉትን የትምህርት ቤት ክፍያውን አለመክፈል፤ ተማሪያችሁ - ከDCPS እንዲታገድ-ለማድረግ በአስጊ ሁኔታ ላይ-ሊጥለው ይችላል። ለማንኛውም

ጥያቄዎች፣ እባክዎን የDCPS የምዝገባ ቡድንን በenroll@k12.dc.govያነጋግሩ።

በDCPS ውስጥ ገብቶ-ለመማር (admission) ሦስት መንገዶች አሉት፤ በመብት (by right)፣ በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት፣ እና በመደበኛ ምደባ (by Formal Placement)። በዋሽንግተን ዲሲ የሚኖር ማንኛውም ዕድሜው የሚያስገድደው ተማሪ፣ ቢያንስ በአንድ ገብቶ-የመማር መብት (right-to-attend) ወይም "በክልል-ወሰን ውስጥ/"in-boundary" - የDCPS ትምህርት ቤት በየ-ክፍል ባንድ (grade band) —ትምህርት ቤቱ በማንኛውም-ሰዓት ለመማር የሚያስችለው መብት አለው። በክልል-ወሰን-ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤታችሁን በሚከተለው-ለይታችሁ-እወቁ https://enrolldcps.dc.gov/node/41. ከመግቢያ መንገዶች (admission methods) ጋር በተያያዘ - ለተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፤ እባካችሁ - የ'DCPS Enrollment and Lottery Handbook'ን ተመልከቱ: https://enrolldcps.dc.gov/node/66።

***አድልዎ አልባ ማስታወቂያ:*** *በስቴት እና በፌደራል ሕጎች መሠረት፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በእውን ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ወይም በሚታሰብ፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በአካላዊ ገጽታ፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በትምህርት ደረጃ፣ በፖለቲካዊ ዝንባሌ፣ በዘር አመጣጥ (genetic) መረጃ፣ በጉዳተኝነት፣ በገቢ ምንጭ፣ በቤተሰብ ትስስር ውስጥ ባለ ወንጀል ሰለባ መሆን፣ ወይም ደግሞ በመኖሪያ ወይም በንግድ ስፍራ፣ አማካኝነት አድልዎ አያደርግም። ሙሉ ጽሁፉን እና ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ http://dcps.dc.gov/non-discrimination* ይጎብኙ።

# የትምህርት ዓመት 2025/2026 የመመዝገቢያ ቅጽ

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

ወደ DCPS ትምህርት ቤት አዲስ ወይም ተመላሽ የሆኑ እያንዳንዱ ተማሪዎችን ለማስመዝገብ **ይህን ቅጽ ይጠቀሙ።** ለ2021/2026 2025 የትምህርት ዓመት ተማሪዎ ወደሚማርበት ትምህርት ቤት፡ ይህንን ቅጽ ያስገቡ። ከዚህ በታች የሚገኙት ጥያቄዎች በሙሉ፣ መመለስ አለባቸው። ይህንን ቅጽ በስገቡ በ**አስር የቀን መቁጠሪያ (calendar) ቀናት** ውስጥ፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክት ነዋሪነትዎ መረጋገጥ እንዳለበት እባክዎን ያስታውሱ።

## የDCPS ተማሪ

**የመጀመሪያ ሥም (First Name):** | **የመጨረሻ ሥም (Last Name):** | **ትውልድ ቀን:**

**የትውልድ ሃገር:** | **የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር (ID):** | **ፆታ:** ❑ ወንድ ❑ ሴት ❑ ከሁለቱም ያልሆነ

**አድራሻ:** | **አፓርትማ:** | **ከተማ/ስቴት:** | **ዚፕ፡**

**የSY 2024/2025 ትምህርት ቤት ወይም ቅድመ ልጅነት ፕሮግራም:** | **ከተማ/ስቴት:**

**የSY 2025/2026 ትምህርት ቤት:** | **የተማሪ ኢሜል:**

**ለትምህርት ዓመት 2025/2026 የክፍል ደረጃ:** *አንዱ ላይ ብቻ ምልክት አድርጉ*
❑ ቅድመ-K3 ❑ ቅድመ-K4 ❑ መዋዕለሕፃናት ❑ 1ኛ ❑ 2ኛ ❑ 3ኛ ❑ 4ኛ ❑ 5ኛ
❑ 6ኛ ❑ 7ኛ ❑ 8ኛ ❑ 9ኛ ❑ 10ኛ ❑ 11ኛ ❑ 12ኛ ❑ የአዋቂ ትምህርት/Adult Education

**የመኖሪያ ሁኔታዎች (Housing Status):** *አንዱ ላይ ብቻ ምልክት አድርጉ*
❑ ቋሚ (የራስ፣ የኪራይ) ❑ ሆቴል/ሞቴል ❑ መጠለያ ❑ ተዳብሎ የሚኖር ❑ መጠለያ የሌለው

**የሚከተለው ተማሪውን ይመለከተዋል?** ❑ አ ❑ የ በማደጎ እንክብካቤ ውስጥ ወይም በመጠባበቅ ላይ ያለ ❑ አ ❑ የ ከማንም ጋር-የማይኖር ወጣት (ቋሚ መኖሪያ ቤት ውስጥ የማይኖር)

**የዝርያ ምደባ (Ethnic Designation):** *አንዱ ላይ ብቻ ምልክት አድርጉ* ❑ ሂስፓኒክ/ላቲኖ ❑ ሂስፓኒክ/ላቲኖ ያልሆነ

**ዘር:** *የሚመለከተውን ሁሉ ምልክት ያድርጉ* ❑ አሜሪካዊ ህንድ/የአላስካ ተወላጅ ❑ እስያዊ ❑ ተወላጅ-ሃዋዪአን/ፓስፊክ አይላንደር ❑ ጥቁር ❑ ነጭ

**ተማሪው የሚከተሉት አሉበት?**
*ለእያንዳንዱ 'አዎ' ወይም 'የለም' ብለው ይምረጡ። ትምህርት ቤቱ ክትትል ሊያደርግ ይችላል።*
❑ አ ❑ የ አለርጂ ❑ አ ❑ የ የሚያስፈልጉ መድኅኒት ❑ አ ❑ የ የአመጋገብ ግደባዎች
❑ አ ❑ የ 504 ዕቅድ ❑ አ ❑ የ IEP ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች

## ወላጅ/አሳዳጊ/ሞግዚት

*መገኘት የሚችለው ሰው-አድራሻ፣ አንድ*

**የመጀመሪያ ሥም (First Name):** | **የመጨረሻ ሥም (Last Name):** | **ከተማሪው ጋር ያለ ዝምድና:**

**ኢሜል:** | **ስልክ:** ❑ ሞባይል/Cell ❑ የቤት ስልክ

❑ ከተማሪው-ጋር አንድ ዓይነት **አድራሻ:** | **ስልክ:** ❑ ሞባይል/Cell ❑ የቤት ስልክ

**አፓርትማ:** | **ከተማ/ስቴት:** | **ዚፕ፡**
❑ ስለተማሪዬ የሚደረግ ግንኙነቶችን በቴክስት/በኢሜል፣ መቀበል እፈልጋለሁ።
❑ በአስፐን (Aspen) ውስጥ፣ የወላጅ ፖርታል (Parent Portal) ማግኛ መንገድ -እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ።

*መገኘት የሚችለው ሰው-አድራሻ፣ ሁለት*

**የመጀመሪያ ሥም (First Name):** | **የመጨረሻ ሥም (Last Name):** | **ከተማሪው ጋር ያለ ዝምድና:**

**ኢሜል:** | **ስልክ:** ❑ ሞባይል/Cell ❑ የቤት ስልክ

❑ ከተማሪው-ጋር አንድ ዓይነት **አድራሻ:** | **ስልክ:** ❑ ሞባይል/Cell ❑ የቤት ስልክ

**አፓርትማ:** | **ከተማ/ስቴት:** | **ዚፕ፡**
❑ ስለተማሪዬ የሚደረግ ግንኙነቶችን በቴክስት/በኢሜል፣ መቀበል እፈልጋለሁ።
❑ በአስፐን (Aspen) ውስጥ፣ የወላጅ ፖርታል (Parent Portal) ማግኛ መንገድ -እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ።

## ስለቤት ውስጥ ቋንቋ የዳሰሳ ጥናት *ወደ DCPS የመጀመሪያ መመዝገቢያዎ ከሆነ ብቻ፣ ይህንን ይሙሉ።*

*ከዚህ በታች ያሉትን ማንኛውም ጥያቄዎች፣ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ሌላ በሆነ ቋንቋ ከመለሳችሁ፤ ልጅዎ - ለእንግሊዘኛ ቋንቋ አገልግሎቶች (English Language Services) እንዲገመገም ይደረጋል። ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባክዎን በቋንቋ እገዛ - ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division) በ202-671-0750 ያነጋግሩ። ስለ እርዳታዎች ለማወቅ:* dcps.dc.gov/service/supports-english-learners-els

**በቤት ውስጥ ቀዳሚ ሆኖ የሚያገለግለው ቋንቋ ምንድነው?** ____________________ *(ቋንቋውን ይግለጹ)*

**ተማሪው አዘውትሮ የሚጠቀመው ቋንቋ ምንድነው?** ____________________ *(ቋንቋውን ይግለጹ)*

**ተማሪው በመጀመሪያ የተጠቀመው፣ ምን ቋንቋ ወይም ቋንቋዎችን ነው?** ____________________ *(ቋንቋውን ይግለጹ)*

**ከትምህርት ቤቱ የሚላኩልዎን መረጃዎች በምን ቋንቋ እንዲደርስዎ ይፈልጋሉ?** *"ሌላ" የሚለው ከተመረጠ፣ የፅሁፍ መላላኩ በእንግሊዘኛ*
❑ እንግሊዘኛ ❑ ስፓኒሽ ❑ አማርኛ ❑ ፈረንሳይኛ

| | |
|---|---|
| *ይሆናል።*<br>*በቃል የማስተርጎም ፣ በማንኛውም ቋንቋ፤ ሲጠየቅ መቅረብ ይችላል።* | ❑ ቻይኒኛ ❑ ቬትናሚዝ ❑ ሌላ:__________________ |

**በአቸኳይ ጊዜ (Emergency) ተጠሪ የሆነ ሰው አድራሻዎች** *የተማሪው ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች መገኘት ካልቻሉ፤ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች በሚፈጠሩ ጊዜ፣ ከዚህ በታች የተገለጸው ሰው(ዎች)ን እናነጋግራለን። ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና በአስቸኳይ ጊዜ ተጠሪ ሆኖ የተመዘገቡ፣ ተማሪውን ከትምህርት ቤት ለመውሰድ (pick up ለማድረግ) ይችላሉ።*

| | | |
|---|---|---|
| **ሙሉ ሥም:** | **ከተማሪው ጋር ያለ ዝምድና:** | **ስልክ:** |
| **ሙሉ ሥም:** | **ከተማሪው ጋር ያለ ዝምድና:** | **ስልክ:** |

**በDCPS ውስጥ የተማሪው ወንድምና እህት** *እባክዎን፣ በማንኛውም የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር፤ ሁሉንም የተማሪውን ወንድምና እህት፣ መረጃ ያቅርቡ።*

| | **ወንድምና እህት 1** | **ወንድምና እህት 2** | **ወንድምና እህት 3** | **ወንድምና እህት 4** |
|---|---|---|---|---|
| **ሙሉ ሥም:** | | | | |
| **ትውልድ ቀን:** | | | | |

**ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ፣ ማረጋገጫ**

እስከማውቀው ድረስ፤ ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። DCPS ይህንን መረጃ በምስጢር በመጠበቅ ለDCPS አገልግሎቶች በሚውል ነገር ብቻ እንደሚጠቀምበት ተረድቻለሁ። ሐሰተኛ መረጃ መስጠት በሕግ የሚያስቀጣ መሆኑን ተረድቻለሁ። ለSY25-26፣ ከአንድ በላይ ትምህርት ቤት ውስጥ ምዝገባውን ይዤ መቆየት እንደማልችል ተረድቻለሁ፤ ስለሆነም፣ ለSY25-26 - ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ትምህርት ቤት ውስጥ መመዝገቤን አረጋግጣለሁ። በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ በነበረኝ የተጠባባቂነት ዝርዝር ምክንያት ቦታውን አግኝቼ ከገባሁ፣ በMy School DC ማመልከቻዬ ላይ ከዚህ ትምህርት ቤት በታች ደረጃ ተሰጥቶኝ በተጠባባቂነት ዝርዝሮች ውስጥ ከነበርኩበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሙሉ የሚሰረዝ መሆኑን ተረድቻለሁ።

**ስም ይፃፍ:** ___________________________________ ፊርማ:_____________________________________ **ቀን**: _______________

**ለት/ቤቱ ስራ ብቻ የሚውል (SCHOOL OFFICIAL USE): Attendance Boundary:** ❑ IB ❑ OOB **| Enroll Method:** ❑ Continuing OR New: ❑ IB ❑ F ❑ P ❑ Lottery ID______________________________________________

# የDC የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ –2025-26 የትምህርት አመት

እርስዎ የግዛቱ ነዋሪ መሆንዎን ለማረጋገጥ እና ስለዚህ እርስዎ ወይም ተማሪዎ በ DC (ዲሲ) የህዝብ ወይም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ብቁ መሆናችሁን ለማረጋገጥ **ይህን ቅጽ ይጠቀሙ።** ሁሉም ቅጾች እና ደጋፊ የነዋሪነት ሰነዶች ለመዝጋቢው ትምህርት ቤት ተሰጥተዋል።

## ደረጃ አንድ፣ እርስዎን በተሻለ የሚገልጽዎትን የነዋሪነት ማረጋገጫ ይምረጡ።

የ DC ነዋሪነትዎን የማረጋገጫ ዘዴዎች ዝርዝር በገጽ ሁለት ላይ ተመልክቷል። ከታች ያሉትን ክፍል 2 እና 3 ከሞሉ በኋላ **አንዱን ይምረጡ።** ከክፍያ ነጻ በ DC (ዲሲ) የህዝብ ወይም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ብቁ ለመሆን፣ 1) አስመዝጋቢው ሰው ተገቢው ሰነድ ያለው ወላጅ፣ አዋቂ ተማሪ፣ ወይም ሌላ የጸና ህጋዊ ሞግዚት፣ አሳዳጊ ወይም ሌላ ዋና ተንከባካቢ መሆን አለበት፣ 2) **አስመዝጋቢው ሰው በኮሎምቢያ ዲስትሪክት <u>በአካል የሚኖር</u> መሆኑን አረጋግጧል**፣ እና 3) አስመዝጋቢው ሰው ነዋሪነቱን የሚያረጋግጥ በህግ እና ደምቦች ላይ በተገለጹት መሰረት የጸና እና ተገቢ የሆነ ሰነድ አቅርቧል።

## ደረጃ ሁለት፣ ስለተማሪው እና አስመዝጋቢው ሰው መረጃ ያቅርቡ።

| **የተማሪ የመጠሪያ ስም፣** | **የተማሪ የአያት ስም፣** | **የትውልድ ቀን፣** |
|---|---|---|
| **የትምህርት ቤት ስም በ 2025-26 የትምህርት ዓመት፥** | | |

| **የሚመዘገብ ሰው** (ገጽ 2 ይመልከቱ) **> የመጀመሪያ ስም፥** | **የአያት ስም፥** |
|---|---|

**እኔ ፡-**
- ☐ የተማሪው ህጋዊ ወላጅ/ሞግዚት/አሳዳጊ ነኝ
- ☐ አዋቂ ተማሪ ነኝ
- ☐ በአዋቂ ተማሪው ፋንታ የሚፈርም ህጋዊ አሳዳጊ ነኝ
- ☐ የተማሪው ሌላ ዋና ተንከባካቢ ስሆን የተሞላ የOPC ቅጽን ሞልቻለሁ
- ☐ አካለመጠን ያልደረሰ ወላጅ እና በመሀላ የተረጋገጠውን የጽሁፍ መግለጫ ሞልተዋል

| **የአስመዝጋቢው አድራሻ፣** | | | **አፓርታማ #፡-** |
|---|---|---|---|
| **ከተማ፣** | **ክልል፣** | **ዚፕ፣** | **የDC ነዋሪነት ፣** ☐ **አዎ** ☐ **አይ** |
| **ኢሜይል፥** | | **ስልክ፣** | |

## ደረጃ ሶስት፣ የነዋሪነት መስፈርቶችን ማረጋገጫ ይፈርሙ።

- እኔ አዋቂ ተማሪ ወይም ህጋዊ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ የማሳደግ ሃላፊነት ያለብኝ ወይም ሌላ ዋና ተንከባካቢ (OPC) መሆኔን እና የጸና እና ተገቢ የነዋሪነት ሰነድ እያቀረብኩ መሆኑን ወይም እኔ እራሴን ነዋሪ አለመሆኔን መግለጼን አረጋግጣለሁ እና የሚያስፈልገውን የትምህርት ቤት የክፍያ ስምምነት እና ለምዝገባ የሚያስፈልገውን የትምህርት ቤት ክፍያን እረዳለሁ።
- እኔ በዲስትሪክቱ በአካል የምኖር መሆኑን ፣ ይህም "ቀጣይነት ላለው ክፍለጊዜ ለመኖር በማቀድ በእውነት የመኖርያ ቦታ በአካል መያዝ እና መኖር" ተብሎ ትርጉም ያለው ነው፣ እና እኔ በ5-A DCMR § 5004 ላይ በተገለጸው መሰረት ነዋሪነቴን ለማረጋገጥ የጸና እና ተገቢ ሰነድ እያቀረብኩ ነው፣ ወይም፣ እኔ እራሴን ነዋሪ እንዳልሆንኩ ገልጫለሁ እና የሚፈለገውን የትምህርት ቤት የክፍያ ስምምነት እና የትምህርት ቤት ክፍያ አጠናቅቃለሁ።
- ለዲሲ የህዝብ ወይም የቻርተር ትምህርት ቤት ምዝገባ የዲስትሪክት ነዋሪነቴን ለማረጋገጥ አላማ ብቻ የተመዘገብኩበትን ማንኛውም በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም (ለምሳሌ ሜዲኬድ፣ ለተቸገሩ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ [TANF] ወይም ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም [SNAP]**)** ለማግኘት የመኖሪያ መስፈርቶችን ለማሟላት ውሳኔ አግኝቼ እንደሆን ይፋ ለማድረግ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ። ከታች በመፈረም ፣ እኔ ይህን እያልኩ ነው፡- እኔ በግል የሚለየኝን መረጃ የግዛት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education, OSSE) የDC ከሌላ ክልል ወይም የፌደራል ኤጀንሲዎች፣ የዲሲ የሰብዓዊ አገልግሎቶችን (Department of Human Services, DHS) ፣ የDC የመኖርያ ቤት ባለስልጣን (DC Housing Authority, DCHA) ፣ እና የጤና እንክብካቤ የፋይናንስ መምሪያ (Department of Health Care Finance, DHCF) እና ሌሎች ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን እንዲወስድ ፍቃድ ሰጥቻለሁ። OSSE መረጃየን ይጠብቃል እና የዚህን መረጃ ጥበቃ እና አጠቃቀም አስመልክቶ ሁሉንም አግባብ ያላቸውን ህጎች ይተገብራል።
- ከላይ ስሙ የተገለጸው ተማሪ በ ኮሎምቢያ ግዛት የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ ወይም ሌሎች በ Columbia (ኮሎምቢያ) ግዛት የገንዘብ ድጋፍ በሚያገኝ ትምህርታዊ አገልግሎቶች የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚመዘገበው እኔ **የሚታመን የቅን ልቦና የDC (ዲሲ) ነዋሪን የምወክል ከሆነ፣ እና በአካል የምኖር መሆኑን በቃለመሀላ የተደገፈ መግለጫ እና ነዋሪነቴን የሚያረጋግጥ የጸና እና ተገቢ የሆነ ሰነድ ካቀረብኩ** ወይም የትምህርት ቤት ክፍያ ስምምነት እና የትምህርት ቤት ክፍያውን ከፈጸምኩ መሆኑን እረዳለሁ።
- የሰጠሁት መረጃ አጥጋቢ ቢመስልም፣ OSSE ወይም የትምህርት ቤት ሀላፊዎች፣ ምክንያታዊ መሰረት ካላቸው፣ የተማሪውን ነዋሪነት ወይም ተማሪውን የሚያስመዘግብ አዋቂ የOPC ሁኔታ ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ ሊፈልጉ እንደሚችሉ እረዳለሁ።
- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ በOSSE አማካኝነት፣ እኔ ነዋሪ አለመሆኔን ከወሰነ ወይም በ 5A DCMR § 5007 መሰረት ፍቃድ የሌለው ነዋሪ መሆኔን ከወሰነ፣ እኔ የተማሪውን ወደ ኋላ የሚሰላ ክፍያ ለመክፈል ሃላፊነት እንደምወስድ፣ እና ተማሪው ከትምርህርት ቤት እንዲለቅ ሊደረግ እንደሚችል እረዳለሁ።
- የሃሰት መረጃ ካቀረብኩ ወደ ዲሲ የወንጀል ክስ ዋና መርማሪ ቢሮ ወይም በሃሰት የይግባኝ ጥያቄዎች ህግ እና ከተማሪ ነዋሪነት ማረጋገጫ ጋር በተያያዘ ለህዝብ ባለስልጣን እያወቀ የተሳሳተ መረጃ የሚያቀርብ ሰው ከ$2,000 የማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ90 ቀናት የማይበልጥ እስራት፣ ነገር ግን በሁለቱም በቅጣት እና በእስራት አይሆንም፣ እንደሚቀጣ በሚደነግገው የዲሲ ኮድ § 38-312 መሰረት ለክስ ወደ ዲሲ የጠበቃ ዋና ቢሮ ልላክ እደምችል ተረድቻለሁ።
- ይህ ቅጽ እና ለዚህ ቅጽ ሁሉም ደጋፊ ሰነዶች፣ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ ሁሉም የሌላ OSSE ቅጾችን ጨምሮ፣ በትምህርት ቤቱ እንደሚያዝ እገነዘባለሁ። ለOSSE፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና ሌሎች የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች፣ የDC የአጠቃላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ እና የDC የአጠቃላይ ጠበቃ ቢሮን ጨምሮ ግን በዚህ ሳይገደብ፣ የዲስትሪክት ነዋሪነቴ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ዓላማ፣ በጥያቄ መሰረት፣ ይፋ እንዲደረጉ ፈቅጃለሁ።
- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪነቴን ለማረጋገጥ በእጁ ያሉትን ምንም ዓይነት የህግ መንገዶችን ሊጠቀም እንደሚችል እገነዘባለሁ።
- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ትምህርት ቤቶች ለመማር ነዋሪነትን ለማረጋገጥ፣ የግብር እና የገቢዎች ቢሮ (OTR) ለ3 የግብር አመታት የገቡ የዲስትሪክት የግብር ሰነዶቼን ገምግሞ እንዲያረጋግጥ እና የዚያን ግምገማ ውጤቶች ለOSSE የምዝገባ እና ነዋሪነት ቢሮ እንዲያቀርብ ፈቃድ ሰጥቻለሁ።
- **እንዲህ አይነት ለውጥ በተደረገ በሶስት የትምህርት ቀናት ውስጥ በራሴም ሆነ በተማሪው የሚደረግ ማንኛውንም የነዋሪነት ለውጥ ለትምህርት ቤቱ ለማሳወቅ ተስማምቻለሁ።**

**አስመዝጋቢው ሰው እዚህ ይፈርም ፣** ______________________________ **ቀን፣** ______________

## ደረጃ አራት ፣ ይህን የተሞላ ቅጽ እና የሚመለከታቸውን ሰነዶች ወደ ትምህርት ቤትዎ ያምጡ።

**ለትምህርት ቤቱ ሀላፊ አገልግሎት ብቻ** የሚከተለው ዘዴ የ Columbia (ኮሎምቢያ) ግዛት ነዋሪ መሆንዎን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ውሏል። አንድ ዘዴ ይምረጡ።

እኔ በቅጣቶች ክስ መሰረት የቀረቡትን ሁሉንም ሰነዶች በግል መመርመሬን እና ከላይ የቀረበው መረጃ በኔ እውቀት፣ መረጃ እና እምነት መሰረት እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ። እኔ በተጨማሪ ሁሉም የዚህ ቅጽ ደጋፊ ሰነዶች በትምህርት ቤቱ የሚያዙ እና ሲጠይቁ ለ OSSE ፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና ሌሎች ኤጀንሲዎች፣ የ DC (ዲሲ) ጠቅላይ መርማሪ ቢሮ እና የ DC (ዲሲ) ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ቢሮ እንደሚሰጥ አረጋግጣለሁ።

**የትምህርት ቤት ሀላፊ ስም (ይጻፉ) ፣** ______________________ **ፊርማ፣** ______________________ **ቀን፣** __________

| **ዘዴ A፣ የትምህርት ቤቱ ባለሟል ያረጋገጠው** | **ዘዴ ለ፡- አንዱን ሰነድ ይምረጡ** | **ዘዴ ለ፡- ሁለት ሰነዶችን ይምረጡ** | ☐ **ዘዴ ሐ፡-** የቤት ውስጥ ጉብኝት |
|---|---|---|---|
| ☐ የOSSE ነዋሪነት ተረጋግጧል (QLIK፣ ASPEN ወይም የCBO ድጎማ) | ☐ የክፍያ ደረሰኝ | ☐ የDC ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ | |
| ☐ የቤት አልባነት ሀብረት ተረጋግጧል | ☐ የDC መንግስት የገንዘብ እርዳታ | ☐ የDC የመንጃ ፍቃድ/ አሽከርካሪ ያልሆነ መታወቂያ | |
| ☐ የዲሲ ወረዳ | ☐ የተረጋገጠ የDC የግብር ቅጽ-D40 | ☐ የቤት ኪራይ ከክፍያ ጋር | |
| ☐ የሚስጥራዊ አድራሻ ፕሮግራም (ACP) | ☐ የሚሊታሪ የመኖርያ ቤት ትእዛዞች | ☐ የፎጅታ ደረሰኝ ከክፍያ ጋር | |
| | ☐ የኤምባሲ ደብዳቤ | | ☐ **ኗሪ ያልሆነ** |

## አስመዝጋቢው ሰው፣ የእርስዎን የ DC ኗሪ ለማረጋገጥ ከሚከተሉት ዘዴዎች (A-C) አንዱን ይከተሉ።

### A

**በትምህርት ቤቱ ባለሟል አማካኝነት ማረጋገጥ።** የቤት እጦት እያጋጠሞት ከሆነ፣ የዲስትሪክቱ ወረዳ እና/ወይም የዲስትሪክት የህዝብ ጥቅማጥቅሞች ፕሮግራም ተሳታፊ ለምሳሌ ሜዲኬድ፣ SNAP ወይም TANF– ትምህርት ቤትዎ አስቀድሞ መረጃዎ ሊኖረው ይችላል። የትምህርት ቤት ባለሟል ወይም የትምህርት ቤቱ የቤት አልባ ላያዘን ጋር ያረጋግጡ።

**በግብር እና ገቢ ቢሮ አማካኝነት ያረጋግጡ (OTR)።** በድጎሚ የሚመዘገቡ ቤተሰቦች/ተማሪዎች ኗሪነታቸውን አብዛኛውን ጊዜ በ OTR የኗሪነት ማረጋገጫ ሂደት ተጠቅመው ማረጋገጥ ይችላሉ። አስመዝጋቢው ሰው በቀዳሚው የበጀት አመት ግብሮች በ(DC) ዲሲ የከፈለ መሆን እና የተማሪ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ያለው መሆን አለበት። ተማሪው በተመሳሳይ የአካባቢ ትምህርት ቤት ኤጀንሲ በድጋሚ የሚመዘገብ እና ከመዋእለህጻናት- 12 ድረስ የሚመዘገብ መሆን አለበት። ወደ ሲስተሙ በ ossedctax.com አማካኝነት ይግቡ። ስኬታማ ከሆኑ፣ ማረጋገጫዎ በትምህርት ቤቱ ለመረጋገጥ ዝግጁ ይሆናል።

### B

**ደጋፊ ሰነዶችን በማቅረብ ማረጋገጥ።** *ሁሉም* እቃዎች በ DC (ዲሲ) የኗሪ ማረጋገጫ ቅጽ ላይ እና የትምህርት ቤቱ የመመዝገቢያ ሰነዶች ላይ እንደተቀመጡት የአስመዝጋቢውን ስም ተመሳሳይ ስም እና አድራሻ ማካተት አለባቸው።

#### ከዚህ ዝርዝር ውስጥ አንድ ነገር ይፈለጋል።

- ይህ ቅጽ በትምህርት ቤቱ ከታየ ጊዜ አንስቶ በ45 ቀናት ውስጥ የተሰጠ የጸና **የክፍያ ሰነድ** ። ለዚህ አመት የ DC (ዲሲ) የግል ገቢ ግብር የተቀነሰበትን ብቻ ማካተት አለበት እና ለተቀናሽ የሌሎች የማናቸውንም ክልሎች ዝርዝር ማካተት የለበትም፣ መጠኑ ዜሮ ቢሆንም እንኳን። በተጨማሪም ላሁኑ የግብር አመት እና ያሁኑ የክፍያ ጊዜ ከዜሮ የሚበልጥ የ DC የግል ገቢ ግብር የተቀነሰበትን ማሳየት አለበት።
- **ከኮሎምቢያ ግዛት መንግስት የተሰጠ ጊዜው ያላለፈበት ኦፊሺያል የገንዘብ እርዳታ ሰነድ፣** ባለፉት 12 ወራት ለተመዝጋቢው ሰው የተሰጠ ሲሆን ለትምህርት ቤቱ ሲቀርብ ወቅቱ ያላለፈበት፣ ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (TANF)፣ Medicaid ፣ ተጨማሪ የዋስትና ገቢ፣ የመኖርያ ቤት እርዳታ ወይም ሌሎች ፕሮግራሞች ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ሳይወሰን አሁን በዚህ ጊዜ ተሰጥቷል።
- **የተረጋገጠ Form D40 (ቅጽ D40 )** በ DC (ዲሲ) የግብር እና ገቢዎች ቢሮ (OTR)የተሰጠ፣ ያሁኑ ወይም ደግሞ በጣም የቅርብ ጊዜ የግብር አመት የ DC ግብሮች የተከፈለበት ማረጋገጫ እና OTR ማህተም ያለው።
- **በወታደራዊ ደብዳቤ ላይ የወታደር የመኖሪያ ቤት ትዕዛዞች ወይም መግለጫ፣** ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የተሰጠ ሲሆን አሁን ለትምህርት ቤቱ በቀረበበት ጊዜ ተሰጥቷል። የመኖሪያ ቤት ማዘዣው ይፋዊ ደብዳቤ መሆን እና ልዩ የዲሲ የመኖሪያ አድራሻን መጥቀስ አለበት። ትዕዛዙ ተመዝጋቢው ግለሰብ በአሁኑ ጊዜ እንደሚኖር መሆኑን እና የመኖር ሃሳብ እንደሌለው ማሳየት አለበት።
- **የኤምባሲ ደብዳቤ** ባለፉት 12 ወራት የተሰጠ። ኦፊሺያል የኤምባሲ ማህተም እና የኤምባሲው ሀላፊ ፊርማ ሊያካትት ይገባል፣ እና አስመዝጋቢው ሰው በሚመለከተው የ DC የትምህርት አመት ላይ በኤምባሲው ንብረት ውስጥ ያለ ወይም የሚኖር መሆኑን ማመልከት አለበት።

**ወይም**

#### ከዚህ ዝርዝር ኁለት የተለያዩ ነገሮች ይፈለጋሉ።

- **የ DC (ዲሲ) የሞተር ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ፍቃድ** ወይም ኦፊሺያል በመንግስት የተሰጠ አሽከርካሪ ላልሆነ የተሰጠ የጸና እና ጊዜው ያላለፈበት መታወቂያ።
- **የ DC ሞተር የተሽከርካሪ ምዝገባ** የጸና እና ጊዜው ያላለፈበት። ጊዜያዊ ምዝገባዎች ተቀባይነት አያገኙም።
- የክፍያ ደረሰኝ፣ የገንዘብ ትዕዛዝ ወይም **የገንዘብ ቼክ ቅጂ የመሰሰሉ የተለየ የኪራይ ክፍያ ማረጋገጫ** የያዘ ህጋዊ እና ጊዜው ያላለፈበት **የኪራይ ወይም የኪራይ ስምምነት (ወታደራዊ ኪራይን ጨምሮ)**።
*የኪራይ ውሉ* የሚጀምርበትን ጊዜ፣ ወርሃዊ የክፍያ መጠን፣ የአከራይ ስም ማካተት አለበት፣ እና በአስመዝጋቢው ሰው እና በአከራዩ የተፈረመ መሆን አለበት።
*የተለየ የክፍያ ማረጋገጫው* ከትምህርት ቤቱ የምርመራ ጊዜ በፊት ወዲያውኑ ባሉት ሁለት ወራቶች መሆን አለበት እና በቤት ኪራዩ ላይ የተገለጸውን ወርሃዊ ኪራይ መጠን ጋር መጣጣም አለበት።
- ***የአገልግሎት ክፍያ (ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ፣ እና የውሃ ደረሰኞች ብቻ ተቀባይነት አላቸው)* ክፍያው የተከፈለ መሆኑን የሚያሳይ ሌላ የተለየ ደረሰኝን**፣ ለምሳሌ የተከፈለበት ሰነድ ፕሪንት፣ የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ፣ ወይም የተመነዘረ ቼክ ቅጂ። *የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኙ* ትምህርት ቤቱ ይህን ቅጽ ከሚመረምርበት ጊዜ ሁለት ወራት ቀደም ብሎ ላለው ጊዜ የተደረገ መሆን አለበት።
*የተለየ የክፍያ ማረጋገጫው* ለተደረገው ክፍያ በተለይ መሆን አለበት። በጣም የተለመደው ነገር ሁለተኛው ደረሰኝ የመጀመርያውን ደረሰኝ ክፍያ የተፈጸመበት የሚያሳይ ሁለት ተከታታይ ደረሰኞችን ማቅረብ ነው። በተጨማሪም የብድር ክፍያ እና የመንግስት ኤጀንሲ የአንድን አገልግሎት ክፍያ መቀነሱን የሚገልጽ ደብዳቤም ተቀባይነት ያላቸው የክፍያ ማረጋገጫ ናቸው። ሁሉም ክፍያዎች መረጋገጥ ያለባቸው ሲሆን ለወደፊት መቀጠር የለባቸውም።

| C | **በቤት ውስጥ ጉብኝት ማረጋገጥ።** እርስዎ ከላይ ባሉት አንዱ ዘዴዎች ማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ስለቤት ውስጥ ጉብኝት ከትምህርት ቤቱ ሀላፊ ጋር ያውሩ። ጉብኝቱ በሚኖሩበት ቦታ መከናወን እና አስመዝጋቢው ግለሰብ እና ተማሪው ቤት ውስጥ እንደሚኖሩ ማሳየት አለበት። |
|---|---|

**ኗሪ ያልሆነ ተማሪ ሆኖ መመዝገብ**

ኗሪ ያልሆኑ ተማሪዎች የግዛቱ የህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ መማር የሚችሉት በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ብቁ የሆኑ የ DC ተማሪዎች ከሌሉ፣ LEA ተማሪውን ለመመዝገብ ከተስማማ፣ ከክልል የትምህርት ቢሮ ዋና ተቆጣጣሪ ጋር የተደረገ ስምምነት ካለ፣ እና የመጀመርያ የትምህርት ክፍያ ከተደረገ ብቻ ነው። የትምህርት ክፍያ ስምምነት እና የትምህርት ክፍያ ለመሙላት፣ እባክዎ ኢሜይል ያድርጉ በ osse.residency@dc.gov ። ኗሪዎች ያልሆኑ በ District's Pre-K Enhancement and Expansion Funding Program (ግዛቱ የቅድመመዋእለ ህጻናት ማሳደጊያ ወይም የማስፋፍያ ድጋፍ ፕሮግራም) መሰረት ለምዝገባ ብቁ አይደሉም።

**ተማሪ ለማስመዝገብ ብቁ የሆኑ ሰዎች።**

- **ወላጅ** - የተፈጥሮ ወላጅ፣ የእንጀራ ወላጅ፣ የቤት ውስጥ አጋር ወይም ተማሪውን በማደጎ የማሳደግ ወይም የመቆጣጠር ስልጣን ያለው ወላጅ፣ የጋራ አሳዳጊን ጨምሮ።
- **ሞግዚት** - ስልጣን ባለው ፍርድቤት የተሾመ የተማሪ ሞግዚት ።
- **አሳዳጊ** - ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አሳዳጊነት የተሰጠው ሰው።
- **ሌላ ዋና ተንከባካቢ** - ከወላጅ ወይም በፍርድ ቤት ከተሾመ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት ውጪ የሆነ ሌላ ዋና የእንክብካቤ አቅራቢ ወይም አብሮት ለሚኖረው ተማሪ ቁጥጥር እና ድጋፍ የሚያደርጉ፣ እና ወላጆቸው፣ አሳዳጊያቸው፣ ወይም ሞግዚታቸው በከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት የሚፈለገውን እንክብካቤ እና ድጋፍ መስጠት የማይችሉ ናቸው።
- **አዋቂ ተማሪ** - እድሜው 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተማሪ፣ ወይም በጋብቻ ምክንያት፣ በህግ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ መሰረት ከወላጅ ቁጥጥር ነጻ የተደረገ ሰው ነው።

# የትምህርት ዓመት 2025-2026 የቴክኖሎጂ ቅጽ

ከፍተኛ ፍጥነት ያለው ኢንተርኔት እና ቴክኖሎጂ ለማግኘት ያላችሁን ደረጃ ለማጋራት፤ **ይህን ቅጽ ተጠቀሙ።**

| የDCPS ተማሪ | | |
|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ሥም (First Name):** | **የመጨረሻ ሥም (Last Name):** | **ትውልድ ቀን:** |
| **የSY 2025-2026 ትምህርት ቤት:** | | |

| የቴክኖሎጂ ማግኛ የዳሰሳ-ጥናት DCPS፣ የሁሉም ቤተሰቦቻችንን የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች ምን-እንደሆነ በመገንዘብ-ላይ እየጣረ-ነው። |
|---|
| **ተማሪዎ ከፍተኛ ፍጥነት ያለው አስተማማኝ የኢንተርኔት መገናኛ <u>በመኖሪያ ቤቱ</u> ውስጥ ሊያገኝ ይችላል?** |
| ❑ **አዎን** |
| ❑ **የለም** |
| **ተማሪዎ <u>በመኖሪያ-ቤት</u> ውስጥ፤ ላፕቶፕ/ታብሌት (laptop/tablet)ን፣ ማግኘት ይችላል? አንዱ ላይ ብቻ ምልክት ያድርጉ።** |
| ❑ **ልጄ፣ በDCPS-የተሰጠ፣ ላፕቶፕ/ታብሌት (laptop/tablet) አለው/ላት** |
| ❑ **ልጄ፣ የግሉ-የሆነ ወይም የDCPS-ያልሆነ ላፕቶፕ/ታብሌት (laptop/tablet) አለው/ላት** |
| ❑ **ልጄ ምንም - ላፕቶፕ/ታብሌት (laptop/table)፣ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ የለውም/ላትም** |

## የቴክኖሎጂ ተቀባይነት ያለው የመጠቀሚያ ፖሊሲ - ስምምነትን-መግለጫ

**የDCPS ለተማሪዎች እና ሠራተኞች፤ የኢንተርኔት፣ የመረጃ ስብስብ (data) እና የኔትወርክ ዘዴዎችን (DCPS network)ን - እንዲያገኙ-ያደርጋል። DCPS በተጨማሪም፣ ለተማሪዎች የኮምፒውተሮች፣ የታብሌቶች፣ እና/ወይም ሌሎች የቴክኖሎጂ ዲቫይሶችን - እንደ ፕሪንተሮች (printers) የመሳሰሉትን (የDCPS ዲቫይሶች ወይም ቴክኖሎጂ) ያቀርባል። የDCPS ኔትወርክ (network) እና የDCPS ቴክኖሎጂ፣ ለተማሪዎች - ለትምህርታዊ፣ ምርምር (research)፣ እና የስራ-መስክ ዕድገት ምክንያት ሲባል የሚሰጡ ናቸው። የ'DCPS Network and DCPS Technology'ን መጠቀም - የሚካሄደው በDCPS የተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ጥቅም - ተገቢ-ሆኖ በሚውል ፖሊሲ (Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy) እዚህ በሚገኘው-አማካኝነት ነው: [https://dcps.tech/aup](https://dcps.tech/aup). የDCPS ዲቫይሶችን፣ ቴክኖሎጂ፣ ወይም ኔትወርክን - ከተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተገቢ-በሆነ መንገድ መጠቀሚያ ፖሊሲ (Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy) ጋር በሚሄድ-ሁኔታ ለመጠቀም-አለመቻል፤ የስነምግባራዊ እርምጃ (disciplinary action)ን ለማስከተል ይችል-ይሆናል። ከዚህ በታች ያለውን ሣጥን-ላይ ምልክት በማድረግ፤ በቴክኖሎጂ ተቀባይነት ያለውን አጠቃቀም ፖሊሲ (Technology Acceptable Use Policy)ን ማንበባችሁን እና መገንዘባችሁን፤ እና በፖሊሲው ውስጥ ለተዘረዘሩት - ለሁሉም ደንቦች እና ሁኔታዎች ስምምነት-ማድረጋችሁን እውቅና-በመስጠት መስማማታችሁን ያሳያል።**

☐ **በዚህ ሣጥን/box ላይ ምልክት-በማድረግ፤ የ'DCPS Technology Acceptable Use Policy'ን ማንበቤን እና መገንዘቤን፣ እና በውስጡ በተዘረዘሩት ደንቦች እና ሁኔታዎች መስማማቴን ያረጋግጣል። እኔ፣ በተጨማሪም - ተማሪዬ የዲሲ ዲቫይሶች፣ ቴክኖሎጂ፣ እና ኔትወርክን ማግኛ-መንገድን እንዲቀበል መፈለጌን-አረጋግጣለሁ። እነዚህ ዕቃዎች በDCPS የባለቤትነት-ንብረት የሆኑ-ሆነው፤ ለተማሪዬ ለትምህርታዊ እና የቀለም-ትምህርት ዓላማ-ጥቅም ላይ ለመዋል ብቻ በተውሶ-የተሰጠ መሆኑን እና በሚጠየቅ-ጊዜ መመለስ-እንዳለባቸው፤ ተገንዝቤአለሁ። ይህን ዲቫይስ ለመመለስ ካልቻልኩኝ፣ ክፍያውን እንድገል የሚያስገድደኝ ሊሆን-ይችላል።**

# የትምህርት ዓመት 2025/2026 ስምምነቶች

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የሚከተሉትን ምርጫዎችዎን ለማሳወቅ **ይህን ቅጽ ይጠቀሙ።** 1) DCPS የተማሪዎን ምስል፣ ድምፅ፣ እና የትምህርት ስራዎች እንዲጠቀም እና፤ 2) የተማሪዎን መረጃዎች ለውትድርና መልማዮች እንዲሰጡ ለማድረግ እና 3) ወደ ተማሪ የሞባይል ስልኮች (cell phones) - በትምህርት-ገበታ የመገኘት ማስታወሻዎች (attendance reminders) ለመላክ - ስምምነት-ውስጥ መግባት።

## የDCPS ተማሪ

| **የመጀመሪያ ሥም** **(First Name):** | **የመጨረሻ ሥም** **(Last Name):** |
| --- | --- |

## በምርጫነት (OPTIONAL) – ለመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) መፍቀድ እና እንዲሰጥ መስማማት

ከዚህ በታች ፊርማዬን በማኖር፤ ለኮሎምብያ ዲስትሪክት፤ ለDCPS፣ እና ለሠራተኞቻቸው እና ወኪሎቻቸው፣የኮንትራክት-ሠራተኞች፣ ተተኪዎቻቸው እና ተመዳቢዎቻቸውን ጨምሮ፤ የሚከተሉትን እንዲያከናውኑ ፈቃድ-ይሰጣል: (1) የተማሪዬን ምስል እና ድምፅ እንዲቀርጹ፣ (2) በራሳቸው ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት የተቀረጹትን ነገሮች፣ እንዲያስተካክሉ (edit እንዲያደርጉ)፣ እና (3) እነዚህን የተማሪዬን የተቀረጹ ምስሎች እና ድምፆች ከጥበብ እና ከጽሁፍ ሥራዎች ጋር በቪዲዮ ቴፕ፣ በፎተግራፎች፣ በዲጂታል ሚዲያ፣ እና በማንኛውም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ወይም የኅትመት ሚዲያ ጭምር፤ (እንደ ፎተግራፎች፣ ዲጂታል ሚዲያ፣ እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ወይም በህትመት መልክ የተማሪውን፣ ምስል፣ ድምፅ፣ የጥበብ ስራ ወይም የፅሁፍ ስራ - እነዚህ በሙሉ በጥቅሉ አንድ-ላይ "ሚዲያ" ተብለው የሚጠቀሱ ላይ) እንዲቀረጹ፣ ከዚህ በታች በመፈረም ፈቃድ ሰጥቻለሁ። ይህን ፈቃድ መስጠት፣ DCPS ወይም የኮሎምብያ ዲስትሪክት ማናቸውንም የልጄን የሕይወት ታሪክ ወይም ሌሎች የግል መለያ የሆኑ መረጃዎችን በተመለከተ ይፋ ለማውጣት ፈቃድ የማይሰጠው ሲሆን፣ ይህን ስምምነት በማንኛውም ጊዜ፣ ትምህርት ቤቴን በማነጋገር መሻር እንደምችል ተረድቻለሁ።

ከዚህ ቀጥዬ፣ DCPS እና የኮሎምብያ ዲስትሪክት፣ ተተኪዎቻቸው፡ እና ተመዳቢዎቻቸውን እና ማንኛውም በህጋዊነት ሚዲያውን የሚጠቀም ሁሉ፣ በዚህ የመልቀቂያ የፈቃደ ስምምነት መሠረት፣ እኔ ወይም ልጄ ካለብን ወይም ሊኖርብን ከሚችል ከማንኛውም ወይም ከሁሉም የይገባኛል ጥያቄዎች፣ ጥፋቶች፣ እዳዎች፣ ክፍያዎች እና ወጭዎች ተጠያቂ ላለማድረግ መልቀቂያ ሰጥተናል። መረጃዎችን የመልቀቅ ሁኔታ በሕግ የተከበረ መሆኑን እገነዘባለሁ። ይህ ስምምነት በማንኛውም የተዘጋጀ ሚዲያ ላይ በዘላቂነት እስከ ዓመቱ ትምህርት ማብቂያ ድረስ የሚያገለግል ስምምነት ሲሆን፤ በማንኛውም ጊዜ፣ በእኔ መሻር ይቻላል።

❑ እስማማለሁ። ❑ አልስማማም።

**ሥም ይፃፍ:** ______________________ **ፊርማ:** ______________________ **ቀን:** ____________

## በምርጫነት (OPTIONAL) – ለውትድርና መልማዮች መረጃዎችን ይፋ ማድረግ (ከ6ተኛ እስከ 12ተኛ ክፍል)

ከዚህ በታች በመፈርም የተማሪ ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ (ወይም ተማሪው ለአቅመ አዳም የደረሰ አዋቂ ከሆነ) መረጃዎች ይፋ ከመስጫው ካልወጡ (opted out) ካላደረጉ በስተቀር፤ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ DCPS የሁሉንም ከ6ተኛ እስከ 12ተኛ ክፍል የተማሪዎችን፣ ስም፣ አድራሻ፣ እና የስልክ ቁጥር ("መረጃ") ለውትድርና አገልግሎት መልማዮች እንዲሰጥ የፌደራል ሕጎች ይጠይቃሉ። ይህ ስምምነት ተማሪዎ በDCPS ተመዝግቦ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን፣ በማንኛውም ጊዜ ስምምነቱን ማገድ ወይም ማንሣት ይቻላል።

❑ DCPS የተማሪዬን/የእኔን (ተማሪው፣ ለአቅመ አዳም የደረሰ ዐዋቂ ከሆነ) መረጃዎች ለውትድርና መልመዮች እንዳይሰጥ እጠይቃለሁ።

**ሥም ይፃፍ:** ______________________ **ፊርማ:** ______________________ **ቀን:** ____________

## በምርጫነት-የሚደረግ (OPTIONAL) – ወደ ተማሪው ሞባይል ስልኮች (Cell Phones) የቴክስት-መልዕክት (ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል)

እኔ፣ ከዚህ-በታች የምፈርመው - የልጄን የሞባይል ስልክ (cell phone) መስጠት በምርጫ-የሚደረግ/optional እና በብቸኝነት ከትምህርት-ገበታ መገኘት-ጋር የተያያዘ ቴክስት/text መልዕክቶችን ለልጄ - ከ6-12ኛ ክፍሎች-ውስጥ ለሚገኘው ለመላክ-ብቻ ጥቅም-ላይ ለመዋል የምሰጥ-መሆኔን ተገንዝቤአለሁ። ጥበቃ-ባለው ማስቀመጫ ውስጥ ይህ መረጃ እንዲቀመጥ ስምምነት-የሰጠሁ እና እንደ "ማውጫ/Directory" መረጃ ለሌላ-ተላልፎ-የሚሰጥ እንዳልሆነ ተገንዝቤአለሁ። በተጨማሪም፤ በእያንዳንዱ የቴክስት (Text) መልዕክት ውስጥ በተካተተው የመውጫ-ደንብን ተጠቅመን - ልጄ ወይም እኔ በማንኛውም ጊዜ - የቴክስት/text መልዕክቶችን ከመቀበል የመውጣት (opt out የማድረግ) መብት እንዳለን አውቀናል።

**የተማሪው ስም እና የሞባይል ስልክ (Cell Phone) ቁጥር:** ______________________ እና ___-___-____.

**ሥም ይፃፍ:** ______________________ **ፊርማ:** ______________________ **ቀን:** ____________

## በምርጫነት-የሚደረግ (OPTIONAL) – የፓኖራማ የዳሰሳ-ጥናት/Panorama Survey መውጫ (Opt-Out ማድረጊያ) (ከ3ኛ እስከ 12ኛ ክፍል)

በበልግ (fall) እና ፀደይ (spring) ወቅት-ላይ፤ DCPS እና የትምህርት ቤት አስተዳደሮች - ተማሪዎች የትምህርት ቤት ተሞክሮአቸውን እንዴት እንደሚመለከቱት ለመገንዘብ እንዲረዳቸው - **ከ3ኛ እና ከዚያ-በላይ ለሆኑ ክፍሎች** - DCPS - የዲስትሪክት-አቀፍ የፓኖራማ የተማሪ የዳሰሳ-ጥናትን ያካሂዳል። የዳሰሳ-ጥናቱ፣ በፍቃደኝነት የሚደረግ እና ሚስጢራዊነትን የጠበቀ ነው። በዳሰሳ-ጥናቱ ላይ፣ አስተማሪዎች - የተማሪያችሁን አማካኝ የውጤት-ደረጃዎችን በተለያዩ ርዕሶች ላይ መመልከት-ይችላሉ፤ ነገር-ግን ለየእያንዳንዱ ጥያቄዎች ተማሪው የሰጠውን መልሶች መመልከት-አይችሉም። የተማሪዎች ስሞች - ስለ የዳሰሳ-ጥናቱ በተመለከተ - በጭራሽ በሪፖርቶቹ ላይ ጥቅም-ላይ አይውልም። የዳሰሳ-ጥናቱ፣ ከ6ኛ እና ከዚያ-በላይ ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ-ተማሪዎችን፣ ስለ ፆታቸው እና ወሲባዊ ማንነት፤ የዳሰሳ ጥናቱ ይጠይቃል። እነዚህ ጥያቄዎች፣ ፆታን የቀየረ (Transgender) እና ፆታ-ያለማረጋገጥ (Gender-Nonconforming) የፖሊሲ መመሪያችንን በተከተለ ሁኔታ፤ ዲስትሪክቱ ለሁሉም ተማሪዎች፣ እኩል የሆነ እንክብካቤን ለማበረታታት ይረዳዋል። እነዚህን ወይም ማንኛውም ሌላ ጥያቄዎችን - ተማሪዎች መዝለል-ይችላሉ።

**ዲስትሪክት-አቀፍ ከሆኑት ዳሰሳ-ጥናቶችን ከመውሰድ ተማሪያችሁ እንዲወጣ/እንድትወጣ (opt-out እንዲያደርጉ) ከፈለጋችሁ፣ እባካችሁ - ይህን ቅጽ ሙሉ:**
የትምህርት ዓመት 2025-26 የፓኖራማ (Panorama) የተማሪ የዳሰሳ-ጥናት መውጫ (Opt-Out ማድረጊያ)። ቅጹ፣ የዳሰሳ-ጥናት ጥያቄዎቹ፣ እና ቀድሞ-የነበሩት ውጤቶች - ሁሉን በdcps.dc.gov/surveys ላይ መገኘት-ይችላሉ።

# የትምህርት ዓመት 2025-2026 ማስታወቂያዎች

ይህ ሰነድ፣ የወላጆችን/የአሳዳጊዎችን እና የDCPS ተማሪያቸውን መብቶች ይዘረዝራል።

## የ2015 የእያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ መሆን ድንጋጌ

ይህ ማሳሰቢያ፣ በ'Title I' ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ተማሪ ያለዎት ወላጅ ከሆኑ፤ በ2015 የእያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ መሆን ድንጋጌ (Every Student Succeeds Act of 2015) መሠረት፣ የተማሪዎን የክፍል ውስጥ አስተማሪን ሙያዊ የብቃት ደረጃቸው-ምን እንደሆነ፣ የመጠየቅ መብት አላችሁ። በማንኛውም ጊዜ፣ የሚከተሉትን መረጃዎች መጠየቅ ይችላሉ:

- አንድ አስተማሪ ለክፍል ደረጃዎቹ እና የትምህርት ዓይነት መስኮቹ፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክትን ብቁነትን ወይም የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን፣
- አንድ አስተማሪ በአስቸኳይ ጊዜ (emergency) ወይም ሌሎች ጊዜያዊ ሁኔታዎች ሲገጥሙ፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክትን ብቁነትን ወይም የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችን በሚያስወግድ መልኩ ያስተምር እንደሆነና እንዳልሆነ፣
- አንድ አስተማሪ የሙያ የምስክር ወረቀት ባገኘበት የትምህርት መስክ ያስተምር እንደሆነና እንዳልሆነ፣
- አንድ ተማሪ አገልግሎቶች የሚሰጠው በሙያው በሚገባ ባልሠለጠኑ (paraprofessionals) (ሥልጠና ባላገኙና በሌላ አስተማሪ የስልጠና ክትትል ሥር ያሉ የአስተማሪ ረዳቶች) መሆን አለመሆናቸው እና፣ ይህ ከሆነ ደግሞ፣ የሙያ ሥልጠና የሌላቸው ረዳቶች የሙያ ደረጃቸው ምን እንደሆነ፣

በአሁኑ-ጊዜ ያለው የDCPS የ'Title I' ትምህርት ቤቶች ዝርዝሮች፤ በhttps://dcps.dc.gov/publication/list-title-i-and-non-title-i-schools ላይ መገኘት ይችላሉ። እባክዎን ሁሉንም ጥያቄዎችዎን እና ማንኛውንም ሌላ ከዚህ ማሳሰቢያ ጋር ተዛማጅነት አለው የሚሉትን ጥያቄዎች፣ ለDCPS - በኢሜል dcps.hrdataandcompliance@k12.dc.gov ወይም በፋክስ በ(202) 535-2483 ይላኩ።

## የተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ

ይህ ማስታወሻ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎችን (ለአቅመ አዳም ደርሰዋል ተብለው የተገመቱ ልጆች ወይም 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ በሆነ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች) የዳሰሳ መጠይቆችን ስለማካሄድ እና ስለ አካላዊ ምርመራዎች/ስለ ማጣሪያዎች እና የግላዊ መረጃዎችን ለገበያ የንግድ አገልግሎቶች የመጠቀም መብቶች ይገልጻል። እነዚህ መብቶች፣ በተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ (Protection of Pupil Rights Amendment) (20 U.S.C. § 1232h; 34 CFR Part 98) ("PPRA") ላይ የተብራሩ ሲሆን፣ በመረጃው ውስጥም እንዲቀርቡ ተደርገዋል። በዳሰሳ ጥናቱ፣ ሥራ-ላይ መዋል እና መረጃዎች አሰባሰብ ላይ፣ የመረጃዎቹን ውጤት ይፋ የማድረግ እና በግላዊ መረጃዎች ለንግድ፣ ለሽያጭ ወይም ለሌላ የስርጭት አገልግሎቶችን በሚመለከት፣ DCPS ፖሊሲዎችን ነድፏል፣ ሥራ ላይም እንዲውሉ አድርጓል። DCPS፣ በዚህ ውስጥ እያለፉ የተጎዱ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ብቁ-የሆኑ ተማሪዎችን፣ ማንኛውንም የጥበቃ-መረጃ የዳሰሳ-ጥናቶችን (ከዚህ በታች ትርጓሜያቸው የተገለጸውን) እና አካላዊ ምርመራዎች (examinations)/የምርመራ-ምልከታዎች (screenings) ለተማሪው መደረጉን በቅድሚያ ያሳውቃል። ለሁሉም አካላዊ ምርመራዎች/ማጣሪያዎች፣ እና ለሁሉም የጽሑፍ (passive consent) ከሚጠይቁ የዳሰሳ-ጥናቶች፤ DCPS ለወላጆች እና ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ስለ ምርመራዎች (examinations)/የምርመራ-ምልከታዎች (screenings) ወይም ስለ የዳሰሳ-ጥናቱ የያዙ-መረጃዎችን ከማስታወቂያቸው ጋር፣ እና በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ተማሪው እንዳይሳተፍ (to opt) ማድረግ እንደሚችሉ፣ የሚገልጽ ማስታወቂያን ያቀርባል። እንደ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ እንደሆነ ተማሪ፣ በPPRA ሥር የሚከተሉት መብቶች ይኖርዎታል:

1. **ለ'ዳሰሳ ጥናቶች/surveys' ስምምነት-መስጠት።** በ'PPRA' ስር፤ በሙሉም ሆነ በከፊል በአሜሪካ የትምህርት መምሪያ (U.S. Department of Education (USDE) የገንዘብ ድጋፍ በሚካሄድበት እና ከሚከተሉት በጥበቃ-የተያዙ የመረጃ ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን - አስፈላጊ የሆነውን የዳሰሳ ጥናት፣ ትንታኔ፣ ወይም ግምገማ ከማስገባታቸው በፊት፤ እና የዳሰሳ ጥናት፣ ትንታኔ፣ ወይም የግምገማ ፕሮግራሞች ላይ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ከማስገባታቸው በፊት ሕጋዊ-የሆነ ስምምነታቸውን መስጠት ያለባቸው:
    - የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ የፖለቲካ ወገናዊነት ወይም እምነት፤
    - የተማሪው ቤተሰቦች አዕምሮአዊ ወይም ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች፤
    - ስለ ወሲባዊ ባህሪያት እና አመለካከት፤
    - ህጋዊነት የሚጎለው፣ ፀረ ማኅበራዊ፣ ራስን የሚያስወነጅል ምስክርነት መስጠት (self-incriminating), ወይም ራስን የሚያዋርድ ባሕሪ ማሳየት፤
    - መልስ ሰጭዎች፣ የቅርብ ቤተሰባዊ ግንኙነቶች ያሏቸው ጋር፤ ስለ ሌሎች የሚሰጡት ወሳኝ ምዘናዎች፤
    - እንደ ከጠበቆች ጋር፣ ዶክተሮች፣ ወይም የቤተ-ክህነት ሰዎች ጋር፣ በሕግ እውቅና የተሰጠው ግንኙነቶችን ማግኘት መቻል፤
    - ሀይማኖታዊ ክንዋኔዎች፣ ትስስር፣ ወይም የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጆች እምነቶች፣ እና
    - የገቢ ምንጭ ሁኔታ፣ ለፕሮግራም-ብቁነትን ለመወሰን በሕግ ከሚያስፈልገው ሌላ።

ምንም እንኳን በ'PPRA' ውስጥ እንደመስፈርት ባይሆንም፤ DCPS ለማንኛውም የዳሰሳ-ጥናት - የገንዘብ-እርዳታ ምንጩ ምንም ሆነ ምን፣ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ተያያዥ የሆኑጥያቄዎች ጋር የሆኑ ክፍሎችን ለማካካወን፤ ህጋዊ የሆነ ስምምነት እንዲኖር ይጠይቃል።

2. **መውጣት (opt out ማድረግ) መቻል።** ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፤ ምንጊዜም ቢሆን፣ ከሚከተሉት ተማሪን የማስወጣት (to opt የማድረግ) እድሎች አሏቸው፤
    - ጥበቃ-ከተደረገባቸው ክፍሎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥያቄዎች የማንጠይቁ - ማንኛውም የዳሰሳ ጥናት፣

- DCPSን ወክለው ምርምር (research)ን የሚያከናውኑ፣ ማንኛውም የተማሪ ክትትል አድራጊ ቡድኖች (focus groups) ወይም በውጪ-አካል የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች፣
- አስቸኳይ ያልሆነ (nonemergency)ማንኛውም የሰውነት አካልን የሚያጋልጥ ምርመራ ወይም ምልከታ (screening)፤ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ለመማር ወይም በወኪሉ አማካይነት የሚከናወን እና ወዲያውኑ ጤንነትን እና ደህንነትን ለመጠበቅ ለተማሪው አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፤ (የመስማት፣ የማየት፣ እና የጀርባ አጥንት መጉበጥ (scoliosis) ማጣሪያዎች እና ማንኛውም የስቴት ሕግ ከሚጠይቀው የአካል ምርመራ/ማጣሪያ በስተቀር)፣ እና
- ማሰባሰብን፣ ይፋ ማድረግን፣ ወይም ወይም ከተማሪዎች ለንግድ ገበያ፣ ሽያጭ፣ ወይም ለማሰራጨት አገልግሎት የተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎችን መጥቀምን፣ (ይህ ለፈፀየእድገት ተግባት፣ ለመገምገም፣ ወይም የትምህርት መጠቀሚያዎችን ወይም አገልግሎቶች፤ ለተማሪዎች ወይም የትምህርት አሰጣጥ ተቋማት ለማቅረብ፤ ማሰባሰብን፣ ማሰራጨት፣ ወይም ከተማሪዎች የተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎችን መጠቀምን ላይ አይመለከተውም)።

3. **የመመርመር መብት።** ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ጥያቄ ሲቀርብ እና ሥራ ላይ ከመዋላቸው ወይም አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት፣ ማጣራት ይችላሉ:
    - ሁሉም የተማሪዎች የዳሰሳ-ጥናቶች፤ ጥበቃ-ከተደረገላቸው ክፍሎች (protected categories) ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ቢጠይቁም-ወይም ባይጠይቁ፤ የገንዘብ-እርዳታ ምንጫቸው፣ እና በDCPS ወይም በሌላ የውጪ አካል መፈጠርና አለመፈጠሩን ማወቅ፤
    - ለማንኛውም ለገበያ፣ ለሽያጭ፣ ወይም ለሌሎች የማከፋፈያ አገልግሎቶች ግላዊ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች፣ እና
    - እንደ ሥርዓተ-ትምህርት አካል ሆነ ለመገልገያነት የሚውል የትምህርት አሰጣጥ ቁሳቁሶች።

መብቶቻቸው ተጥሷል ብለው የሚያምኑ ወላጅች/አሳዳጊዎች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች፤ በሚከተሉት አድራሻዎች የአቤቱታ-ክሶችን ማቅረብ ይችላሉ: የ'Family Policy Compliance Office'፤ U.S. Department of Education, 400 Maryland Avenue, S.W., Washington, DC 20202.

## የወላጅ የትምህርት መብቶች እና የግል መረጃዎች የመጠበቅ መብት ድንጋጌ

የወላጅ የትምህርት መብቶች እና የግል መብት ድንጋጌ (The Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA) ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና እድሜአቸው 18 እና ከዚህ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ("ብቁ የሆኑ ተማሪዎች") የተማሪን የትምህርት መረጃዎች በሚመለከት የተወሰኑ መብቶች አሏቸው። ይህ የጽሁፍ ሰነድ በግልጽና በዝርዝር የተቀመጡ፡ ያለዎትን በጣም አስፈላጊ መብቶች ለማሳወቅ የቀረበ ነው:

1. **የተማሪውን የትምህርት መረጃዎች የመርመር እና የማጣራት መብት** በ45 ቀናት ውስጥ - DCPS፣ መረጃዎቹን ለማግኘት ጥያቄ ይደርሰዋል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ለመርመር የሚፈልጉትን(ጓቸውን) መረጃዎች የሚገልጽ የጽሑፍ ጥያቄ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ሌላ ተገቢ የሆነ የትምህርት ቤት ባለሥልጣን መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል ሁኔታዎችን በማመቻቸት ወላጅን/አሳዳጊን ወይም ብቁ የሆነን ተማሪ መረጃዎቹ የሚመረመሩበት ጊዜ እና ቦታ ያስታውቃል ወይም የተጠየቁት መረጃዎች ከሌሉም ያስታውቃል።
2. **የተማሪውን የትምህርት ማስረጃዎች እንዲስተካከሉ የመጠየቅ መብት** ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ሆኖ የሚገኝ ተማሪ በFERPA ሥር የትምህርት ማስረጃዎቹ ትክክል አይደሉም ወይም አሳሳች ናቸው ወይም የተማሪውን የግል መብት ያዛባሉ ብሎ የሚያምኑ ከሆነ። ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ሆኖ የሚገኝ ተማሪ፤ በሰነዱ ክፍል-ላይ እንዲለወጥ ስለሚፈልጉትን፣ እና መለወጥ ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ - ግልጽ የሆነ-ጽሁፍን ወደ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ማስገባት አለባቸው። በወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ በሆነው ተማሪ እንደ ተጠየቀው፣ DCPS መረጃውን ላለማስተካከል ከወሰነ፣ ትምህርት ቤቱ ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ለሆነው ተማሪ፣ ስለ ውሳኔው በመንገር ለማስተካከል ስለተጠየቀው ጉዳይ በችሎት እንዲታይላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ይመክራቸዋል። ስለፍርድ ሂደቶቹ (hearing procedures)፣ ተጨማሪ መረጃችን ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ሆኖ ለሚገኝ ተማሪ፤ በፍርድ እንዲታይ ለማድረግ ያላቸው መብታቸው በሚገለጽላቸው ጊዜ እንዲያውቁ ይደረጋል።
3. **የግል መለያ የሆኑ መረጃዎች ይፋ እንዲወጡ (በጽሁፍ) የመስማማት መብት** በተማሪው የትምህርት መረጃዎች ውስጥ የሚገኙትን መዝገቦች፤ FERPA ያለስምምነት ይፋ ሊያወጧቸው ስልጣን እስከተሰጣቸው ድረስ እስካሉት በስተቀር። ለምሳሌ፣ ተማሪው ለመመዝገብ በሚፈልግበት ወይም በተመዘገበበት ትምህርት ቤት እና የተማሪውን የትምህርት መረጃዎች ይፋ ማድረግ ለተማሪው ምዝገባም ሆነ ለዝውውር ተግባር አገልግሎት በሚጠየቅበት ጊዜ፤ DCPS ያለስምምነት ለሌላ ትምህርት ቤት ወይም ለሌላ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ ለሚገኙ ሥልጣናት መርጃዎቹን ይፋ ያደርጋል። በተጨማሪም፣ DCPS ህጋዊ ትምህርት ነክ ዝንባሌዎች ይኖራቸዋል ብሎ ለሚያስባቸው ባለሥልጣናት FERPA የትምህርት መረጃዎች ያስምምነት ፈቃድ ይፋ እንዲወጡ ሊያዝ ይችላል። የትምህርት ቤት ባለሥልጣን በDCPS አስተዳዳሪ፣ ተቆጣጣሪ (supervisor)፣ አስተማሪ፣ ወይም ረዳት የሥራ አባል ሆኖ የተቀጠረ ሠራተኛ (የጤና ወይም የህክምና ባለሙያ እና የሕግ አስከባሪ አባል ሠራተኞችን ጨምሮ)፣ DCPS፣ ልዩ ሥራ እንዲያከናውን የተኮናተረው (እንደ የሕግ ጠበቃ፣ ኦዲተር፣ የህክምና ባለሙያ፣ ወይም ቴራፒስት (therapist) የመሳሰሉትን)፣ እንዲያከናውን የተኮናተርው ሰው ወይም ኩባንያ፣ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ፣ ተማሪ ወይም ለምሳሌ በሥነ-ሥርዓት ወይም አቤቱታ-ሰሚ ኮሚቴ ወይም በሕጋዊ ኮሚቴ፣ ወይም ኃላፊነቱን ወይም ኃላፊነቷ ለመወጣት ለሚያገለግል ወይም ለምታገለግል ለሌላ ትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ሥራ የሚያግዝ ተማሪ ወይም ሌላ የበጎፈቃድ ሠራተኛ ነው። ሙያዊ-ኃላፊነታቸውን ለመወጣት - የትምህርት ሰነዶችን ለማሟላት ምልከታ-ማድረግ ካስፈለጋቸው፤ የትምህርት ቤት ባለ-ሥልጣን - ህጋዊ የትምህርታዊ ፍላጎቶች አላቸው።
4. **አቤቱታ የማቅረብ መብት** የአሜሪካ (U.S.) የትምህርት መምሪያ ከFERPA ጋር መሟላት የሚገባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት DCPS አላሟላም ተብሎ የተከሰሰበትን ጉዳይ በሚመለከት። 'FERPA' የሚያስተዳድሩ ጽህፈት ቤት ስም እንእ አድራሻ-እንደሚከተለው ናቸው፤ 'Family Policy Compliance Office'፣ 'U.S. Department of Education'፣ 400 Maryland Ave. SW, Washington, DC 20202.
5. **ተማሪውን የስም ማውጫ መረጃዎች (directory information) ይፋ እንዳይወጡ የመጠየቅ መብት።** በራሱ ውሳኔ፣ DCPS መሠረታዊ

የሆኑ “የስም ማውጫ መረጃዎችን (directory information)”፣ በአጠቃላይ ጎጂ ናቸው ተብለው የማይታዩ፣ ወይም ካለወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን ስምምነት ሳይሰጥ ግላዊነትን መጣስ አይደለም የተባሉትን፣ በዲስትሪክቱ ሕግ እና በFERPA ድንጋጌ መሠረት ሊሰጥ ይችላል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች፣ ከዚህ በታች የሚገኘውን የተማሪ የማውጫ መረጃ (Directory Information) የሆነው የመልቀቅ ክፍል በአስር (10) የተማሪው የምዝገባ የትምህርት ቀናቶች ውስጥ ሞልቶ በማጠናቀቅ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ማንኛውንም ወይም ሁሉንም መረጃዎችን፣ DCPS እንዳይሰጥ ትዕዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ። ከዚህ በታች ያለው መልቀቂያ (release)፣ በአስር (10) የምዝገባ የትምህርት ቀናቶች ውስጥ ካልቀረበ፤ ከዚህ በታች የተሰጠው መረጃ፣ እንደ ተማሪዎ የማውጫ መረጃ (directory information) ሆኖ ለቀሪው የትምህርት ዓመት እንዲመደብ እንደተፈለገ አድርጎ DCPS በመገመት የሚወስደው ይሆናል።

## በምርጫነት (OPTIONAL) – የተማሪ የስም ማውጫ (Directory) መረጃን አለመስጠት

DCPS፤ ይፋ-የሚያወጣውን መረጃ ለመገደብ፣ መምረጥ ይችላሉ። ያለ እርስዎ ስምምነት DCPS ከዚህ በታች ይፋ እንዲያደርጋቸው የማይፈልጓቸው መረጃዎች ካሉ፣ እባክዎን ምልክት ያድርጉባቸው:

- ❑ የተማሪ ስም
- ❑ በይፋ የታወቁ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርቶች መካፈል
- ❑ የተቀበሏቸው ዲፕሎማዎች/ሽልማቶች
- ❑ የተማሪ አድራሻ
- ❑ የአትሌቲክ የቡድኖች አባላትን ክብደት እና ቁመት
- ❑ በትምህርት-ገበታ የተገኙባቸው (Attendance) ቀናት
- ❑ የወላጅ/አሳዳጊ ኢሜል
- ❑ ከዚህ በፊት የተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ስም
- ❑ የተማሪ የስልክ ቁጥር ዝርዝር
- ❑ የክፍል ደረጃ
- ❑ የተማሪ የትውልድ ቀን እና የትውልድ ቦታ
- ❑ የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም

ከዚህ በታች በመፈረም፣ የሚከተሉትን አረጋግጣለሁ:

- DCPS ከላይ ምልክት ያደረኩባቸውን የሚመለከት ምንም ዓይነት መረጃን ይፋ አያደርግም፣
- ምልክት ያላደርኩባቸውን ማናቸውንም መረጃዎች፣ ከዚህ ቀጥዬ DCPS ይፋ ሊያደርግ እንደሚችል ተስማምቻለሁ፣ እና
- ምልክት ካደረኩባቸውም ውስጥ ቢሆን፣ DCPS አሁንም ቢሆን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ወይም ደግሞ በFERPA የተፈቀደ ሆኖ ከተገኘ፣ ይህንን መረጃ ይፋ ሊያደርግ እንደሚችል ተገንዝቤአለሁ።

**የተማሪ ስም:** ________________________________________ **የወላጅ/አሳዳጊ ስም:** _______________________________

**ፊርማ:** _____________________________________________ **ቀን:** _______________________________________________

DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

# የዲሲ ትምህርት ቤት የክትባት መስፈርቶች መመሪያ

*ከ07-18-2024 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል-2024*

**ይህ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ልጆች ወደ ቁልፍ ክፍሎች እንዲገቡ የሚያስፈልጋቸው ክትባቶች ማጠቃለያ ነው። የ ✓ ቁጥር በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ለመግባት የሚያስፈልገው ጠቅላላ ዶዝ ብዛት ነው። ስለ መስፈርቶቹ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ በdchealth.dc.gov/immunizations ላይ ይገኛል።**

| የቅድመ–መዋእለ–ህጻናት–መዋእለ–ህጻናት3* ለመጀመር | መዋእለ–ህጻናት ለመጀመር | 7ኛ ክፍል ለመጀመር | 11 ኛ ክፍል ለመጀመር |
|---|---|---|---|
| DTaP ✓✓✓✓ | DTaP ✓✓✓✓✓ | DTaP ✓✓✓✓✓ | DTaP ✓✓✓✓✓ |
| ፖሊዮ ✓✓✓ | ፖሊዮ ✓✓✓✓ | ፖሊዮ ✓✓✓✓ | ፖሊዮ ✓✓✓✓ |
| ኩፍኚ ✓ | ኩፍኚ ✓✓ | ኩፍኚ ✓✓ | ኩፍኚ ✓✓ |
| MMR ✓ | MMR ✓✓ | MMR ✓✓ | MMR ✓✓ |
| ሄፓታይተስ ቢ (Hepatitis B) ✓✓✓ | ሄፓታይተስ ቢ (Hepatitis B) ✓✓✓ | ሄፓታይተስ ቢ (Hepatitis B) ✓✓✓ | ሄፓታይተስ ቢ (Hepatitis B) ✓✓✓ |
| ሄፓታይተስ ኤ (Hepatitis A) ✓✓ | ሄፓታይተስ ኤ (Hepatitis A) ✓✓ | ሄፓታይተስ ኤ (Hepatitis A) ✓✓ | ሄፓታይተስ ኤ (Hepatitis A) ✓✓ |
| ኒሞኮካል (PCV) ✓✓✓✓ | | Tdap ✓ | Tdap ✓ |
| ሄሞፊለስ ኢንፍሉዌንዛ አይነት ቢ (Haemophilus Influenzae Type B) (Hib) ✓✓✓(✓) ጥቅም ላይ የዋለው የብራንድ ዓይነት ላይ በመመርኮዝ | | HPV ✓ | HPV ✓✓ |
| | | ሜኒንጎኮካል (Meningococcal) ✓ | ሜኒንጎኮካል (Meningococcal) ✓✓ |

✓ = የዶዞች ቁጥር

***የቅድመ–መዋእለ–ህጻናት3 ልጅዎ እድሜያቸው 4 አመት ሲሞላቸው MMR፣ Chickenpox፣ Polio እና Diphtheria/Tetanus/Pertussis ላይ ተጨማሪ የክትባት ዶዞችን ለመውሰድ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን በሰዓቱ እንዲያገኙ በጣም እናበረታታለን፣ነገር ግን እነዚህ በአመቱ አጋማሽ ላይ ካለው የክትትል (መገኘት) መስፈርት ጋር አይቀጠሩም።**

# ሁሉ-አቀፍ የጤና የምስክር ወረቀት

DC HEALTH GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA | GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

ይህን ቅጽ ይጠቀሙ የልጅዎ አካላዊ ጤናን ለትምህርት ቤታቸው/የልጅ እንክብካቤ ተቋማቸው ሪፖርት ለማድረግ። ይህ በዲሲ ኦፊሴላዊ ኮድ §38-602 የሚጠየቅ ነው። ፈቃድ ያለው የህክምና ባለሙያ ክፍል 2 - 4 እንዲሞላ ያድርጉ። የጤና መድን ፕሮግራሞችን በ dchealthlink.com ያግኙ። በልጅዎ ትምህርት ቤት በዋና ቢሮ በኩል የጤና ቡድን ሰዎችን ሊያነጋግሩ ይችላሉ።

## ክፍል 1፥ የልጅ የግል መረጃ | በወላጅ/አሳዳጊ የሚሞላ።

| | | |
|---|---|---|
| **የልጅ የአያት ስም፥** | **የልጅ የመጀመሪያ ስም፥** | **የትውልድ ቀን፦** |

| | | |
|---|---|---|
| **የትምህርት ቤት ወይም የልጅ እንክብካቤ ተቋም ስም፥** | **የተማሪው የክፍል ደረጃ፦** | **ጾታ፦** ☐ ወንድ ☐ ሴት ☐ ወንድም ሴትም ያልሆነ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የቤት አድራሻ፦** | **Apt፦** | **ከተማ፡** | **ስቴት፥** | **ZIP (ዚፕ)፣** |

**ብሄር፦** *(የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ)፦* ☐ ሂስፓኒክ/ላቲኖ ☐ ሂስፓኒክ-ያልሆነ/ላቲኖ-ያልሆነ ☐ ሌላ ☐ የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ

**ዘር፦** *(የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ)* ☐ አሜሪካ ህንዳዊ/የአላስካ ተወላጅ ☐ እስያዊ ☐ የሀዋይ ተወላጅ/ የፓሲፊክ ደሴት ተወላጅ ☐ ጥቁር/ አፍሪካ አሜሪካዊ ☐ ነጭ ☐ መልስ ላለመስጠት እመርጣለዉ

| | |
|---|---|
| **ወላጅ/የአሳዳጊ ስም፥** | **የወላጅ/የአሳዳጊ ስልክ ቁጥር፥** |
| **የአደጋ ጊዜ ተጠሪ ስም፥** | **የአደጋ ጊዜ ተጠሪ ስልክ ቁጥር፥** |
| **የመድን ዓይነት፥** ☐ Medicaid ☐ የግል ☐ ምንም የለም | **የመድን ስም/መታወቂያ ቁጥር #፥** |

**ባለፈው ዓመት ውስጥ ልጁ/ጅቷ የጥርስ ህክምና ሀኪም/የጥርስ ህክምና አቅራቢ ጋር ሄደዋል?** ☐ አዎ ☐ አይ

ፈራሚው የጤና መርማሪ/ተቋም በዚህ ቅጽ ላይ ያለውን የጤና መረጃ ለልጄ ትምህርት ቤት፣ የልጅ እንክብካቤ፣ ካምፕ፣ ወይም ተገቢ የዲሲ መንግስት ኤጀንሲ እንዲያጋራ ፈቃድ እሰጣለሁ። በተጨማሪም፣ ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሠራተኞቹ እና ኤጀንቶቹ በዲሲ ሕግ 17- 107 ስር ለድርጊቶች ወይም መታለፎች ከህግ ተጠያቂነት ነጻ እንደሚሆኑ እነሆ እውቅና እሰጣለሁ እናም እስማማለሁ፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ የታሰበበት ጥፋት፣ ከፍተኛ ቸልተኝነት፣ ወይም በፈቃድ የሚደረግ የስነ-ምግባር ጉድለት ከሆነ በስተቀር። ይህ ቅጽ በየዓመቱ ተሞልቶ ወደ ልጄ ትምህርት ቤት መመለስ እንዳለበት እረዳለሁ።

ወላጅ/ሞግዚት ፊርማ፥ ______________________________ ቀን፦ ____________________

## ክፍል 2፥ የልጅ ጤና ታሪክ፣ ምርመራ፣ እና ምክረ-ሀሳቦች | ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ አቅራቢ የሚሞላ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **የጤና ምርመራ ቀን፥** | **BP:** ____/____ ☐ NML ☐ ABNL | **ክብደት፥** ☐ LBS ☐ KG | **ቁመት፥** ☐ IN ☐ CM | **BMI፥** | **BMI ፐርሰንታይል፦** |

**የእይታ ምርመራ ብቃት ደረጃ፦** ከ 3–6 አመት ለሆኑ ልጆች፣ (አልፏል/ወድቋል) ብቻ አስፈላጊ ነው።
6 አመት እና በላይ ለሆኑ ለዚህ ክፍል የእይታ ብቃት ደረጃ ያስፈልጋቸዋል።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **የእይታ ማጣሪያ፥** | የግራ ዓይን፥ 20/______<br>የቀኝ ዓይን፥ 20/______<br>ግራ፦ ☐ አልፏል ☐ ወድቋል<br>ቀኝ: ☐ አልፏል ☐ ወድቋል | ☐ ተስተካክሏል<br>☐ አልተስተካከለም | ☐ መነጽሮችን ይለበሱ | ☐ ሪፈር ተደርጓል | ☐ አልተመረመረም |

**የመስማት ምርመራ፦** *(የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ)* ☐ አልፏል ☐ ወድቋል ☐ አልተመረመረም ☐ መሳሪያ ይጠቀማል ☐ ሪፈር ተደርጓል

**ልጁ/ልጅቷ ከሚከተሉት የጤና ስጋቶች ማንኛውንም አለው/አላት?** *(የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ እና ዝርዝሮችን ከታች ያቅርቡ)*

- ☐ አስም
- ☐ ኦቲዝም
- ☐ ባህሪያዊ
- ☐ ካንሰር
- ☐ ሴሬብራል ፐልሲ
- ☐ የእድገት
- ☐ የስኳር በሽታ
- ☐ መቋቋም አለመቻል
- ☐ የልብ ድካም
- ☐ የኩላሊት በሽታ
- ☐ የቋንቋ/ንግግር
- ☐ ከመጠን ያለፈ ውፍረት
- ☐ ስኮሊዮስስ
- ☐ የሚጥል በሽታ
- ☐ ሲክል ሴል
- ☐ ድንገተኛ የህክምና እንክብካቤ ሊያስፈልጋቸው የሚችሉ ጉልህ የምግብ/የመድሃኒት/የአካባቢ አለርጂዎች። *ዝርዝሮች ከታች ቀርበዋል።*
- ☐ የረጅም-ጊዜ መድሃኒቶች፣ ያለ-ሀኪም ትዕዛዝ የሚገዙ መድሃኒቶች (ኦቨር-ዜ-ካውንተር-ድራግስ (OTC)) ወይም የልዩ እንክብካቤ መስፈርቶች። *ዝርዝሮች ከታች ቀርበዋል።*
- ☐ ጉልህ የጤና ታሪክ፣ ሁኔታ፣ ተላላፊ በሽታዎች፣ ወይም ውስንነቶች። *ዝርዝሮች ከታች ቀርበዋል።*
- ☐ ሌላ:- ____________________

**ዝርዝሮችን ያቅርቡ። ልጁ/ጅቷ Rx/ህክምና ካገኘ/ች፣ እባክዎ የተሟላ የመድሃኒት/የጤና ህክምና እቅድ ቅጽን ያያዙ፤ እና ልጁ/ጅቷ ሪፌር ተደርጎ/ጋ ከሆነ/ች፣ እባክዎ ማስታወሻ ይያዙ።**

**የTB ግምገማ |** ፖዘቲቭ የሆነ TB ለግምገማ ወደ ተቀዳሚ የእንክብካቤ ሰጪ ሪፈር መደረግ አለበት። ለጥያቄዎች የ DC Health የጤና ቁጥጥርን በ 202-698-4040 ያግኙ። የሳንባ ነቀርሳ ላይ ለተጨማሪ መረጃ dchealth.dc.gov/page/tuberculosis-basics ይጎብኙ።

| ለ TB የልጁ/ልጅቷ የስጋት ደረጃ ምንድን ነው? | የቆዳ ምርመራ ቀን፥ | | IGRA የደም ምርመራ ቀን፦ | |
|---|---|---|---|---|
| ☐ ከፍተኛ > *ሙሉ የቆዳ ምርመራ እና/ወይም IGRA የደም ምርመራ ያድርጉ*<br>☐ ዝቅተኛ | **የቆዳ ምርመራ ውጤቶች፥** | ☐ ኔጌቲቭ<br>☐ ፖዘቲቭ፣ CXR ኔገቲቭ<br>☐ ፖዘቲቭ፣ CXR ፖዘቲቭ<br>☐ ፖዘቲቭ፣ የታከመ | **IGRA ውጤቶች፦** | ☐ ኔጌቲቭ<br>☐ ፖዘቲቭ<br>☐ ፖዘቲቭ፣ የታከመ |
| **የ TB ምርመራ ላይ ተጨማሪ ማስታወሻዎች፥** | | | | |

**የሊድ ተጋላጭነት ስጋት ማጣሪያ |** ሁሉም የሊድ ደረጃዎች ለዲሲ የልጅነት ሊድ መመረዝ መከላከያ ሪፖርት መደረግ አለባቸው። በ 202 ይደውሉ ወይም በ 481-3837 ፋክስ ያድርጉ።

| **እድሜያቸው ከ6 ዓመት በታች ለሆነ ህጻናት ብቻ**<br>*ሁሉም ህጻናት 2 ዓመት እድሜ ሲሞሉ 2 የሊድ ምርመራዎች ማድረግ አለባቸው* | **የ1ኛ ምርመራ ቀን፥** | **የ1ኛውጤት፥** | ☐ ጤናማ<br>☐ ጤናማ ያልሆነ፣<br>**የእድገት የምርመራ ቀን፦** | **1ኛ የሴረም/የጣት ስቲክ ሊድ ደረጃ** |
|---|---|---|---|---|
| | **የ2ኛ ምርመራ ቀን፥** | **የ2ኛውጤት፥** | ☐ ጤናማ<br>☐ ጤናማ ያልሆነ፣<br>**የእድገት የምርመራ ቀን፦** | **2ኛ የሴረም/የጣት ስቲክ ሊድ ደረጃ፥** |
| | **የ3ኛ ምርመራ ቀን፥** | **የ3ኛውጤት፥** | ☐ ጤናማ<br>☐ ጤናማ ያልሆነ፣<br>**የእድገት የምርመራ ቀን፦** | **3ኛ የሴረም/የጣት ስቲክ ሊድ ደረጃ፥** |

# ሁሉ-አቀፍ የጤና የምስክር ወረቀት

DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

## ክፍል 3፡ የክትባት መረጃ | ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ አቅራቢ የሚሞላ።

| **የልጅ የአያት ስም፥** | **የልጅ የመጀመሪያ ስም፥** | | | | **የትውልድ ቀን፦** | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ክትባቶች** | **ከታች ያለው ሳጥን ውስጥ፣ የክትባት ቀናትን (ወወ/ቀቀ/ዓዓ) ያቅርቡ** | | | | | | |
| ዲፍቴሪያ፣ ቴታነስ፣ ፔርቱስስ (DTP, DTaP) | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | |
| DT (<7 ዓመታት)/ Td (>7 ዓመታት) | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | |
| የTdap ጨማሪ | 1 | | | | | | |
| DTaP-IPV | 1 | 2 | | | | | |
| DTap-IPV-Hib | 1 | 2 | 3 | | | | |
| DTap-HepB-IPV | 1 | 2 | 3 | | | | |
| DTap-IPV-Hib-HepB | 1 | 2 | 3 | | | | |
| ሄሞፊለስ ኢንፍሉዌንዛ ዓይነት b (Hib) | 1 | 2 | 3 | 4 | | | |
| ሄፓታይትስ B (HepB) | 1 | 2 | 3 | 4 | | | |
| ፖሊዮ (IPV፣ OPV) | 1 | 2 | 3 | 4 | | | |
| ሚዝልስ፣ ማምፕስ፣ ሩቤላ (MMR) | 1 | 2 | | | | | |
| ሚዝልስ | 1 | 2 | | | | | |
| ማምፕስ | 1 | 2 | | | | | |
| ሩቤላ | 1 | 2 | | | | | |
| ቫሪሴላ | 1 | 2 | ልጅ የዶሮ በሽታ (ቺኪን ፖክስ) ነበረው (ወር እና ዓመት)፥<br>የተረጋገጠው በ፥ ______________________________ (ስም እና ማዕረግ) | | | | |
| ኒሞኮካል ኮንጁጌት | 1 | 2 | 3 | 4 | | | |
| ሄፓታይትስ A (HepA) (በ 01/01/2005 ወይም በኋላ የተወለደ) | 1 | 2 | | | | | |
| ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) | 1 | 2 | 3 | | | | |
| ሜኒንጎኮካል ክትባት (ACWY) | 1 | 2 | | | | | |
| ኢንፍሉዌንዛ (የሚመከር) | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| ሮታቫይረስ (የሚመከር) | 1 | 2 | 3 | | | | |
| COVID-19/ኮሮናቫይረስ (የሚመከር) | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| ሌላ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |

☐ ልጁ/ጅቷ **ለክትባት ወደ ኋላ ቀርቷል/ቀርታለች** እና መልሶ ወደ ጊዜ ሰሌዳ እርሱን/እርሷን/እነርሱን ለመመለስ የተቀመጠ እቅድ አለ።
**የሚቀጥለው ቀጠሮ፥** ______________________________________________________

# ሁሉ-አቀፍ የጤና የምስክር ወረቀት

DC HEALTH GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA | GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

**የህክምና መታለፍ (የሚመለከተው ከሆነ)**
ከላይ የተገለጸው/ች ልጅ በጊዜ ለሚከተሉት ክትባት ለመውሰድ ትክክለኛ የሆነ የህክምና የማይወስድበት/የማትወስድበት ሁኔታ(ዎች) እንዳለው/ላት አረጋግጣለሁ፥

☐ ዲፍቴሪያ ☐ ቴታነስ ☐ ፔርቱስስ ☐ Hib ☐ HepB ☐ ፖሊዮ (ሁሉም 3 አይነቶች) ☐ሚዝልስ
☐ ማምፕስ ☐ ሩቤላ ☐ ቫሪሴላ ☐ ኒሞኮካል ☐ HepA ☐ ሜኒንጎኮካል (Meningococcal) ☐ HPV
☐ COVID-19/ ኮሮናቫይረስ

**ይህ ክትባት ለመውሰድ ትክክለኛ የሆነ የህክምና የማይወስድበት/ የማትወስድበት ሁኔታ ጊዜያዊ ነው?** ☐ ዘላቂ ☐ ጊዜያዊ ነው እስከ፥ ______________________(ቀን)

**በበሽታ ያለመያዝ አማራጭ ማረጋገጫ (የሚመለከተው ከሆነ)**
ከላይ የተጠቀሰው/ች ልጅ በሚከተሉት ያለመያዝ የላቦራቶሪ ማስረጃ እንዳለው/ላት አረጋግጣለሁ እናም የምርመራ ውጤቶች ቅጂን አያይዛለሁ።

☐ ዲፍቴሪያ ☐ ቴታነስ ☐ ፔርቱስስ ☐ Hib ☐ HepB ☐ ፖሊዮ (ሁሉም 3 አይነቶች) ☐ ሚዝልስ
☐ ማምፕስ ☐ ሩቤላ ☐ ቫሪሴላ ☐ ኒሞኮካል ☐ HepA ☐ HPV

## ክፍል 4፥ ፈቃድ ያለው የጤና ስራ የሚሰራ የምስክር ወረቀት | ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ አቅራቢ የሚሞላ።

ይህ ልጅ በትክክል ምርመራ ተደርጎለታል/ላታል እና የጤና ታሪክ ተገምግሞ በዚህ ቅጽ ላይ በተዘረዘሩ ይዘቶች መሰረት ተመዝግቧል። በምርመራው ጊዜ፣ ይህ ልጅ በሁሉም የትምህርት ቤት፣ ካምፕ፣ ወይም የልጅ እንክብካቤ ተግባራት ውስጥ ለመሳተፍ **አጥጋቢ የጤና ሁኔታ** ላይ ነው ያለው/ያለችው፣ በገጽ አንድ የተገለጸው ከሆነ በስተቀር። ☐ አይ ☐ አዎ

ይህ ልጅ **ለውድድር ስፖርቶች** ተጣርቶ/ታ አልፏል/አልፋለች። ☐ NA ☐ አይ ☐ አዎ ☐ አዎ፣ ተይዞ ያለው ተጨማሪ የመልቀቂያ ቅጽ፥ ______________________

ይህን ልጅ እንደመረመርኩ እና እዚህ ውስጥ የተመዘገበው መረጃ በምርመራው ውጤት ምክንያት የተወሰነ እንደሆነ እዚህ አረጋግጣለሁ።

**ፈቃድ ያለው የጤና እንክብካቤ አቅራቢ የቢሮ ማህተም**

**የአቅራቢ ስም፥**

**የአቅራቢ ስልክ ቁጥር፥**

**የአቅራቢ ፊርማ፥**

**ቀን፡-**

## ለቢሮ ስራ ብቻ | ሁሉ-አቀፍ የጤና የምስክር ወረቀት በትምህርት ቤት ባለስልጣን እና የጤና ቡድን ሰራተኞች የሚቀበል ነው።

**የትምህርት ቤት ባለስልጣን ስም፥**

**ፊርማ፡-** **ቀን፡-**

**የጤና ቡድን ሰራተኛ ስም፥**

**ፊርማ፡-** **ቀን፡-**

# የ አ ፍ ጤና ግም ገማ ቅ ጽ

እድሜያቸው  3ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሁሉም ተማሪዎች፣ የአፍ ጤንነት ሁኔታቸውን ለትምህርት ቤታቸው/የልጅ እንክብካቤ ተቋማቸው ሪፖርት ለማድረግ ይህንን ቅጽ ይጠቀሙ።

DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

## መመሪያዎች

- ከዚህ በታች ያለውን ክፍል 1 ይሙሉ። ይህንን ቅጽ ለልጅ/ተማሪ የጥርስ ህክምና አቅራቢ ይስጡ። የጥርስ ህክምና አቅራቢ ክፍል 2ን መሙላት አለበት።
- ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ እና የተፈረመውን ቅጽ ለተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት/የልጅ እንክብካቤ ተቋም ይመልሱ።

## ክፍል 1፦ የልጅ/ተማሪ መረጃ (በወላጅ/አሳዳጊ የሚሞላ)

የመጀመሪያ ስም ______________________ የአያት ስም ____________________________ የመካከለኛ ስም የመጀመሪያ ፊደል __________

የትምህርት ቤት ወይም የልጅ እንክብካቤ ተቋም ስም________________________________________

የተማሪ መታወቂያ ቁጥር _________________________ (ወወቀቀዓዓዓዓ)፡ የትውልድ ቀን ☐☐/☐☐/☐☐☐☐

አሁን ያለው የጾታ ማንነት፡ ____________________

የቤት አድራሻ፡ ________________________________ የመኖሪያ ስቴት፡ ______ የመኖሪያ የዚፕ ኮድ ☐☐☐☐☐

| ትምህርት ቤት ክፍል | የቀን- እንክብካቤ | የቅድመ- መዋዕለ- ህጻናት 3 | የቅድመ- መዋዕለ- ህጻናት 4 | መዋዕለ- ህጻናት | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | የአዋቂ ትምህርት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

## ክፍል 2፦ የልጅ/ተማሪ የአፍ ጤና ሁኔታ (በጥርስ ህክምና አቅራቢው የሚሞላ)

| | አዎ | አይ |
|---|---|---|
| 1. ታካሚው **ግልጽ የሆነ መቦርቦር** (ያልታከመ የጥርስ መበስበስ) ያለበት ቢያንስ አንድ ጥርስ አለው/አላት? ይህ ምንም ግልጽ የሆነ የኢናሜል መዋቅር ብልሽት ወይም ያልተዳረሰ ዲሚኒራላይዝድ ቁስሎችን (ማለትም ነጭ ነጠብጣቦችን) የቆሸሸ ጉድጓድ ወይም ስንጥቅ አያካትትም። | ☐ | ☐ |
| 2. ይህ ታካሚ ቢያንስ አንድ **የታከመ የተበሰበሰ ጥርስ** አለው/ላት? ይህ እንደ ጥርስ መበስበስ ህክምና ውጤት አማልገም፣ ኮምፖሲት፣ ጊዜያዊ ወደ ቦታ መመለሶች፣ ወይም ክራውንስ ያለበት ማንኛውም ጥርስን ያካትታል። | ☐ | ☐ |
| 3. ታካሚው/ዋ ቢያንስ አንድ **በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተያዘ ማሸጊያ** ዘላቂ የመንጋጋ ጥርስ አለው/ላት? | ☐ | ☐ |
| 4. ታካሚው/ዋ **ከመደበኛ ምርመራው/ዋ በፊት እንክብካቤ የሚያስፈልገው** ያልታከመ መበስበስ ወይም ሌላ የአፍ **ጤና ችግር አለው/ላት? (የቅድመ እንክብካቤ አስፈላጊነት)** | ☐ | ☐ |
| 5. ታካሚው/ዋ **ህመም፣ እብጠት፣ ወይም ማበጥ** አለው/ላት? **(የአስቸኳይ እንክብካቤ አስፈላጊነት)** | ☐ | ☐ |

6. የታካሚው/ዋ አፍ ውስጥ በመበስበስ የተጎዱ ስንት **የመጀመሪያ ጥርሶች** አሉ፣ ከሚከተሉት አንዱ የሆነ፡
   - **a. ያልታከመ** ☐☐
   - **b. በመሙላት/በክራውንስ የታከመ?** ☐☐
7. የታካሚው/ዋ አፍ ውስጥ በመበስበስ የተጎዱ ስንት **የዘላቂ ጥርሶች** አሉ፣ ከሚከተሉት አንዱ የሆነ፡
   - **a. ያልታከመ** ☐☐
   - **b. በመሙላት/በክራውንስ የታከመ** ☐☐
   - **c. በመበስበስ ምክንያት የተነቀለ?** ☐☐
8. ታካሚው/ዋ ምን ዓይነት የጥርስ ህክምና መድን አለው/ላት? Medicaid ☐ የግል መድህን ☐ ሌላ ☐ ምንም የለም ☐

የጥርስ ህክምና የአቅራቢ ስም ________________________________________ የጥርስ ህክምና ማህተም

የጥርስ ህክምና የአቅራቢ ፊርማ ________________________________________

የጥርስ ህክምና ምርመራ ቀን ________________________________________

ይህ ቅጽ ከዚህ በፊት የነብረውን ለዲሲ ትምህርት ቤቶች፣ ሁሉም የአስቀድሞ ማስጀመሪያ ፕሮግራሞች፣ እና የልጅ እንክብካቤ ማዕከላት መግቢያ ያገለግል የነበረውን የዲሲ የአፍ ጤና ምርመራ ቅጽን ይተካል። ይህ ቅጽ በDC Health የጸደቀ እና ሚስጥራዊ ሰነድ ነው። ምስጢራዊነት ለጤና አቅራቢዎች የወጣውን የ1996 (HIPPA) የጤና መድን ማንቀሳቀሻ እና ተጠያቂነት ህግ እና ለዲሲ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች አቅራቢዎች የወጣውን የቤተሰብ ትምህርት መብት እና ግላዊነት ህግን (FERPA) የሚከተል ነው።